
ከሦ ዓመት በኃላ ወደ እናት ሀገሩ
የተመለሰው መጽሐፍ

ራእየ ባሮክ



በግዕዝና በአማርኛ የተዘጋጀ
መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ መንግስቱ ጥላሁን
አዲስ አበባ ፳፻፲ ዓ.ም
ሦስተኛ እትም

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ፍኖ

በስመ አብ።ወወልዱ።
ወመንፈስ።ቅዱስ።ዕ
ለምለም ሩቤል ዘስር
አዮኤመዚአ-ብሔር ዕ
ቅዱስ።ሠርክ አምድ
ዜረኩ ሄ።ሶሎሞ ፫ወሶ
ዓመሥ።ወሸዲ-ሃ ስዑ
ሠ።ወአመ-ኤ ሄ ሩሰሌ
ም።ወሃ ቅ ምሥ ቅዱ
ሠ።ሊቅ ከህ ት-ሥ።ዘ
ስመ-።አ ሰ።አስ ግ ፯ድ
ር ስዕ ወ ደ ሞ ር።ሣ ሰ።አ
ዛ ዊ።ኃ ዋ ዓ ሠ።ቅ ወ ነ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

All right reserved

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
ትምህርት ሥርዓትና ደንብ መሠረት የተዘጋጀ

1. አንደኛ አትም ፲ሀየገፀ ዓ.ም
2. ሁለተኛ አትም ፳፻፩ ዓ.ም
3. ሦስተኛ አትም ፳፻፫ ዓ.ም

ይህ የግብጻዊው አድራሻ ነው::

SAMEHSAAD AZOUZE
33MOHAMMED EL SAGHIER
OLD CAIRO
CAIRO
EGYPT TEL 3651936 HOME

ማውጫ

ገጽ

መክሰተ አርዕስት

ሀ. መቅድም ..... ፪

ለ. መግቢያ ..... ፭

ሐ. ለተርጓሚው አባት ያለኝ መልሰክት ..... ፮

መ. መታሰቢያነቱ ..... ፱

ሠ. ምስጋና ..... ፲

፩፣ ራእየ ባርነ. ምሰራዊ አንድ ..... ፲፩

፪. ጸሎት " በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እሰከ በሰላመ ቅዱስ ንብርኤል" ..... ፶፩

Scanned by DocumentScanner | Lufick

መቅድም

ባሿ ዓመቱ ወደ እናት ሀገሩ የተመለሰው ታሪካዊው መጽሐፍ

ራዕየ ባርክ

እዝየ ታሪኩ እንዲህ ነው በ ፲፱፻፭ ዓ.ም በንዳር ዙር ውስጥ በግብጽ ሀገር ከሚኖሩ የተዋሕዶ እምነት ተከታዮች የሆኑት በግብጽ የቅድስተ ማርያም ስንዝት ት ቤት ተማሪዎች በረኛው ዓመት በዓል እስክራቸው ላይ እንድገኝ ይጋብዙኛል። በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት ያለምንም እንቅፋትና ችግር በአንድ ሳምንት ውስጥ ፓስፖርቴን በማሳደስ ከግብጽ ኤምባሲ ቪዛ በማግኘት ጎዳር ፲፰ ቀን ፲፱፻፲፭ዓ.ም ግብጽ ገባሁ። ጌታም ፈቃዱ ሆኖ በደመቀውና የተዋሕዶ መንፈን በተጉናጸፈው የሰንዝት ት ቤቱ በነበል አስባበር ላይ ለመገኘት ቻልኩ። በቆየሁባቸውም ጊዜያት ውስጥ በግብፅ የማገኙ ታሳላቅና አስገራሚ ገጻግቶን በተለይም እመቤታችን ጊታን ታቅፋ (ይዛ) የተጓዴተተችበትን ቦታና ቁስቋም ገዳምን ሳይቀር አስጉብኙኝ። የሰንዝት ት ቤቱ ኃላፊዎች፣ አባቶች፣ ኮሚቲዎች፣ አመራሮች፣ ወንድሞች፣እህቶች በጠቅሳሳ ልጆቿ የሆኑት ሁሉ ያደረጉልኝ አቀባበልና መስተንግዶ ለዘላለም የማይረሳ ነው ።

ይህም ብቻ ሳይሆን እመቤታችንን ቅዱስ ዮሴፍን ሰሎሜንና አሀያሞን ወደደ ጨራት የደበቀቻቸውን ታሪካዊ ሾላ ስንጉበኝ አስጉብኙዎች ታሪኩን ሲነግሩን በእንባ እናዳምጥ ነበረ፡ በየጊዜው የዕለተ ዓርብንና የዕለተ እሑድን የወንጌል መርሐ ግብር ሳይነካ በጠቅሳሳ ብዙ ታሳላት ነገሮችን እንደ ቁስድም አባ እንጦስ አባ ቡሳ ሠለስቱ መቃርስን የመሳሰሉትን ገዳማት አስጉብኙተውናል።

በዚሁ በጉብኝታችን ወቅት በታሳቁ በማር ጊዮርጊስ ገዳም በግብጽ ከተማ ውስጥ ሲያስጉበኙኝ አንድ ግብጻዊ የተዋህዶ እምነት ተከታይ የሆነ ይህን የብራና መጽሐፍ አምጥቶ ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ነው፡ እነሱን ጠይቅ ብለውኛል ሲል በእንግሊዘኛ ቋንቋ አናገረኝ እኔም ከየት አገኘከው ብዬ አጠገዜ ካሉት ወንድሞቼ ጋር ጠየቅሁት ግብጻዊውም ሰው ይህ መጽሐፍ አባቴ እጅ ከገባ ፱ ዓመቱ ነው አሁን ግን አባቴ ሞቷል ይህ ቅዱስ መጽሐፍ ኃይል አለው እስከ ዛሬ ለብዙ ሰዎች አሳይቻለሁ መጽሐፉን ሲቀበሉኝና ሲገልጡት ያንቀጠቅጣቸዋል (They became hot and lose it) ወድያውኑ ሊንቀጠቀጡ ከእኛቸው ይወድቃል አያናግሩኝም ጥለውትና ጥለውኝ ይሄዳሉ ይህ መጽሐፍ በእውነት የኢትዮጵያ መጽሐፍ ነው? አለኝ። እኔም አዘረውኝ ካሉትም ወንድሞቼ ጋር በመሆን አዎን የኛ ነው አልኩት ተርጉምልኝ ምንድ ነው አለኝ ይህ ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል ነው በጣም ከባድ ነው የጻፈውም "ባርኩ" የተባለ የእግዚአብሔር ሰው (ነቢይ) ነው ይህንንም መጽሐፍ የሚተረጉሙት በታሳላት ገዳማት የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸው። የእግዚአብሔርን ቃል የሚተረጉምም የሚናገርም የእግዚአብሔር ሰው መሆን አለበት ብዬ የሚያሳምን መልስ ከሰጠሁት በኋላ ስጠኝ ብለው ፈቃደኛ አለመሆኑ ግልጽ ስለሆነ ፎቶ ኮፒ ከሙሉ አድራሻህ ጋር ስጠኝና አስተርጉሜ እልክልሃለሁ ስሰው ፈቃደኛነቱን ሲገልጽልኝ ደስታዬ መሰን አልነበረውም። ምክንያቱም ይህ ቅዱስ መጽሐፍ ከእናት

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ለዘለዓለም አይተውንም በጉድለት አጠባበቅው የነበረው የዚህ ታሪካዊ
መጽሐፍ፡ የቀጠርው ቀንና ሰዓት ደረሰ ተገናኘን ያግብፃዊ በእምነት
እንድ የሆነው የተዋሕዶ ልጅ ወንድሜ "ራዕዩን" ይዘ ብቅ አለ ደስ
አለኝ ከነሙሉ አድራሻው ሰጠኝ ። ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና
ይግባውና መጽሐፉን ተቀብዬ ከሦስት ወራት ቆይታ በኋላ የካቲት ፲፮
ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ወደ አናት ሀገሬ ገባሁ የቀደሙት አባቶቻችን
(አበው) "የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ" ይላሉ፡ እዳንጠፋ
እንጠንቀቅ። በግብጽ ምድር ደግሞ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ታላቅና
የሚያኮራ ስም አለን ። ይኸውም ጥቁር አይዋሽም ይላሉ ። ታዲያ
ይህን ስማችንና ክብራችንንም የለበውንም ቃል ለመጠበቅ ይህን
መጽሐፍ ለማስተርጉም ትልቅ ጥረት አደረግሁ። ለግብጻዊዉ
ወንድሜ ትርጉሙን ለመላክ መስንዘሁ። የልብን ምኞት የሚፈጽም
ልዑል እግዚአብሔር ጊዜውና ፈቃዱ ስለደረሰ መጽሐፉ ተተርጉሞ
ወገኖቹ ለሆኑት ለኢትዮጵያውያን የሚደርስበት ሰዓቱና ጊዜው አሁን
በመሆኑ በምወዳችው ወገኖቹ !
በወንድሜ በኖ ር ይልማ አያሉውና
በእውቱ በወ ሮ ስሎሜ አስፋ አማካይነት
በርዕስ አድባራት ዓምደ ሃይማኖት በደብረ ሊባኖስ በታላቁ ገዳም
የሚኖሩትን ታላቁን የመጽሐፍት ሊቅ መምህር ጥበቡ ገ/ማርያምን
አገናኝተውኝ የመጽሐፉን ታሪክ ነግሬ አማክርኳቸው። እኝህ ታላቅ
የቤክርስቲያን አባት በፍቅርና በትሕትና ሆነው፡ በሚጣፍጥና
በማይጠገብ አንደበታቸው አነጋገሩኝ።

ሆኩ በተለደደ በሃ ዓመት ወደ ሀገሩ ለመመለስ የነበዩ የባርክ አምላክ
እኔን ምክንያት በማድረጉ ፍቶ ከርሙን እንስቶ እዳ እስከሚደርስ
ድረስ ዙሙአቤ ጊታን አማበነው ነበር። ለዚህም ያለትስ ነበር። በሌላ
በኩል ቤሕሊናዬ የዚህች ታላቅ ሀገርና የውዲቷ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያናችን ውድ ቅርሶቿ አባቶችንን በመንፈስ ቅዱስ
አየተመሩና አየተቃች ሠርዓትና በንጹሕ ልቦናቸው የጻፏቸው የብራና
መጻሕፍት ለትውልድ ይናሩ ዘንድ ያስቀመጧቸውን ንብረቶች እንደ
ደውዳ አፈብቸውን በገንዘብ የሸው ሚልፊቶችና አደጣጥ የአንድ ሀገር
ቅርስ የወገኝ የሆዝ ክራት እንደሆን የማይገባቸው ጭንጋፎች
የመሬት ሽሙና የታሪክ አተላዎች እግዚአብሔር ይፈርድብናል ሀገርና
ወገን ይወቅስናል ላይሉ የቤተክርስቲያንና የውድ እናት ሀገራቸውን
ቅርስ እየዘረፉና እየሰረቁ ምንነቱን ለማያረዳ ሰባሰድ ይታዘበናል
እኚን ላይሉ የሸጡትንና የተሸጡትን የሀገሬን ቅርስ ቤሕሊናዎ
ላውጣና ላወርድ እንደ እገር አባት ውስጤ ሲቀጠል ሕሊናዬ
ሲቀሰል ኢትዮጵያ ! የ ግዚአብሔር ሀገርናትና ንብረቶቿ ሁሉ
የተሰረቀውና የተዘረፈው ሁሉ የእግዚአብሔር ንብረት ነውና
የተወሰዱት ቅርሶቿ ሁሉ ይልዑል ግዚአብሔር ፈቃድና አስገዳጅነት
እንድ ቀን ይልየዩ ወደ እናት ሀገሩ ይመለስና ይዝከሰብ ይሆናል
ምክኒት ውኒታዎች እያለውና ራሴን በራሴ በዚህ አጽናንቼ ቤሉላብ
ከምታወልዳት ንሰር ሀገር ወደራሴ ተመለስኩ። ይህ ጉናና የሆንና
ታላቅ አምላክ እንድ ሥራ ለኢትዮጵያ እንደሚሠራ ተስፋም አደረግሁ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

በተለይም የውዲቷ ሀገራችንና የታላቋ የተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያናችን ቅርስ እየተዘረፈና እየተሰረቀ ወደ ባዕድ ምድር መወሰዱና መሸጡ ሀገራቸውንና ወገናቸውን ለሚወዱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የሕሊና ቁስል ነው፡ በማለት በረጋ እንደበታቸው ኃዘናቸውን ከነገሩኝ በኋላ ይህን በዓ ዓመቱ ለእናት ሀገሩ መልክን ምድር የበቃውን መጽሐፍ ሰጠኋቸው። ተቀበሉኝ። እሳቸውም ከተመለከቱት በኋላ የዚህን ታላቅ ነቢይ ራዕይ በመተርጉም ከፍተኛ እርዳታና ድጋፍ አድርገውልኛል፡ እኔም ከፍያለ ምስጋና በልዑል እግዚአብሔር ስም አተርባለሁ።

ውድ ወገኖቼ

ልዑል እግዚአብሔር በተፈጥሮ፣ በእበው፣ በነቢያት ፣በሐዋርያትና፣ በሊቃውንት ፣አድሮ አንዲሠ፣ም በየጊዜው ሰውን የሚያስነሣው እኛን ከገቢረ ኃጢአት ወሞ ገቢረ ጽድቅ፣ ከክህደት ወደ እምነት እያንዳንዳችንን ለመመለስና፡ መጻሕፍት ቢጻፉና ቢተረጐሙ እንድንመከርበት፣ እንድንማርበት ብሉም እንዲፈረድብን በመሆኑ ጌታ ይህን ለነቢዩ የገለጸውን ራእይ ተምረን ፣አንብበንና አውቀን (ራእይ) እንድንጠቀምበት ጌታ በወሰነው፡ ጊዜና ወቅት የቅርሱ፣ ባለቤት ለሆነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታትሞ ለመቅረብ በቅቷል። ይህም ጌታን ያነጋገረና በመልኡኩ ይመራ የነበረው የታላቁ ነቢይ መጽሐፍ ተተርጉሞ ለአናንተ ለወገኖቼ በመቅረቡ እንዲሁም ወደ እናት ሀገሩ በቅርስነት ለመመለሱ ምክንያት በመሆኔ ታላቅ ደስ ይለማኛል እኳን ደስ አለን።

ውድ ወገኖቼ

ኢትዮጵያን የረገጠ ነጭ ባዶ እጁን አያመለስምና በየባዕድ አገሩ እንዲህ ያለ ነገር ቢገዛመን በፎቶ ኮፒ እንኳን ቢሆን ቅርሳችንን ለመለዋወጥ ጥረት እናድርግ።

የእናቱ ልጅ!

በየዕለቱና በየወቅቱ የሚዘረፈው የቤ/ክርስቲያናችንና የሀገራችንን ቅርሶች እኛው በኛው በመሆኑ ለመጠበቅ አልቻልንምና ሌላው ይቀር ስለ እግዚአብሔር ቤት ስለ እግዚአብሔር ሀገርና ንብረት መደፈር እንዘንና እናልቅስ! ንናናውና ሕያው እግዚአብሔር እንደዚህ መጽሐፍ አንድ ቀን የጠላውና የተሰደደው ወገናችንን ጠቅላላ ቅርሳችንን ሁሉ ይመለሰው ይሆናል።ራእየ ባሮክ ወደ እናት ሀገሩ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የመፈጸሙ ተዓምር አለ? ሕያው እግዚያብሔርን ሠርቷልIII እየሰራም ነው።

የእናቴ ልጅ!

ከዚህ በላይ ምንም አልልም ጊዜያችን ነጋዲዎች የበዙበት ስለሆነ ለሁሉም አሜን ባሮክ(የባሮክ አምላክ) ከብሩን ይግለጥለት(ያሳየው) እሜንIII

"እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር" ::

ልዑል እግዚአብሔር የወጣውን ሁሉ እንደወጣ አያስቀርብን፡ አሜን

መጋቢ ሃይማኖት ቀሲስ መንግሥቱ ጥላሁን

ሦስተኛ አትም ፳፻፲ ዓ.ም

Scanned by DocumentScanner | Lufick

መግቢያ

ይህ መጽሐፍ ሰኖ እንዲደርስና ሕይወት እንድናገኝበት ከተሰደደበት አገር ወደ እናት አገሩ መልሶታል፡ ይህ ራዕይ ተተርጉሞ በዚህ ዘመን ላለነው ኢትዮጲያውያን እንዲደርሰን ተደርጓል። እንብበንና ተረድተን መታረሙና መጠቀሙ የኛ ፋንታ ነው፡ ከዚሁ መጽሐፍ ጋር የጸሎት መጀመሪያችን የሆነው "ከበስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" እስከ በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል አብሮ ታትሟል በዚህ መጽሐፍ ጸሎት ምን ማለት እንደሆነ እንረዳው ዘንድ እኝሁ አባት ከራሳቸው ጨምረው የሰጡኝ ሲሆን ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ በባለ ራዕዩና በተርጓሚው ድካም ሰማዕያንና አንባብያን እንድንጠቀምበት ይርዳን።

ከአዘጋጁ መጋቤ ሃይማኖት ከቀሲስ መንግስቱ ጥላሁን

በ፲፱፻፺፮ ዓም መስከረም ተተረጎመ
በ፲፱፻፺፱ ዓም በወርኃ ግንቦት ታተመ
ተርጓሚ መምህር ጥበቡ ገ/ማርያም
አዘጋጅ መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ መንግሥቱ ጥላሁን

ለተርጓሚው አባት ያለኝ መልክት

ለውድ አባታችን ለመምህር ጥበቡ ገ/ማርያም እርስሥን ካገኘሁበት ዕለት አንስቶ የማይረሱ ብዙ ነገሮችን ገብያቻለሁ ካፈሯቸውና በመንፈስ ከወለዷቸው ልጆችም ዝናዎትንና ድካሞን አይቻለሁ ለምቻለሁ። የድካምዎም በረከት ደርሶኛል፡ ከልጆችዎ ጋር አንዴ ለመባል እግዚአብሔር የደመረኝ ይመስለኛል፡ እንዲሁም የዋሕነትን፣ ትሕትናን፣ ፍጹም ፍቅርንና፣ ሰው መውደድን፣ አለመሰልቸትን ከገዝብና ከውዳሴ ከንቱ መራቅን ጌታ ፈቃዱ ሆኖ ክርስም ለማየት በቅቻለሁኝ።

ከእግዚአብሔር እና ከአባቶችም ያገኙትን ያደለቡትንና የሰበሰቡትን ሰውተት ለወገኖችም በተለይም ለዚህች ቤ/ክርስቲያን መብራትና ዕንቁ የሆኑትን መምህራን አፍርተዋል፡ ደክመዋል እየደከሙም ነው፡ ውድ አባታችን እንግዲህ የእርስዎ የድካምዎ ዋጋ በሰው እጅ አይደለምና በጻድቃን ከተማ (አደባባይ) ለቅዱሳኖቹ ዋጋቸውን ሊሰጥ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ቀንና ዕለት ዋጋዎን እንዲከፍሉት ምኞቴ የላቀና ወሰን የሌለው ነው።

ያስተማረውን አባቱንና ያስተማረችውን እናቱን (እናት ሀገሩን) የማይረሳ ልጅ አይባልም (እርሱ ይሙት) ውድ አባታችን የማቴሳላን ዕድሜና ጤና ይስጥዎ።

ከሁሉ ታናሽ የምሆን ልጅዎ
መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ መንግሥቱ ጥላሁን

መታሰቢያነቱ

በሸዋ ክፍለ ሀገር ልዩ ስሙ ወሊሶ ግዮን በምትባለው ከተማ ለብዙ ዓመታት ድውያን ሥጋን በማጥመቅ ድውያነ ነፍስን በማስተማር ከአሥር ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ለፈወሱትና ከእናት ጡት በላይ በሚጣፍጠው ትሕትና በተሞላበትና በወንጌል በታነጸው ሕይወታቸው በነበሩበት ዘመን በደረሰብኝ ፈተና ሁሉ በተዋሕዶ ሃይማኖት እንድጠነክርና እንድጸና ላደረጉኝና ላስተማሩኝ ምንጊዜም በሕይወቴ ለማልረሳቸው ውድ አባታችን፡ ለብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ (አባ ወልደ ትንሣኤ ግዛው) ይሁንልኝ እሁንም በዚሁ ቦታ በእግዚአብሔር ቸርነት በአባታችን ጸሎትና አማላጅነት ብዙ ድውያን ድኅነት እያገኙ ነው።

በረከታቸው ከሁላችን ጋር ይሁን። አሜን!
መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ መንግሥቱ ጥላሁን

Scanned by DocumentScanner | Lufick

መግቢያ

ድ

ምስጋና

፩ ይህን መጽሐፍ ለተረጐሙት አባት

፪ ለሕትመት እንዲበቃ በኮምፒዩተር የመለተሙንና የመጻፉን ሁኔታ ለረዱኝ፡ ሀ. ወ/ሮ ትዝቲት ኃይሉ

ለ. ወ/ሮ ሃይማኖት ተስፋዩ እንዲሁም በተቾላቸው ሁሉ ለተባበሩኝና እንዲሁም

ሐ. ለወ/ሮ አዜብ ተስፋዩ

መ. ወ/ሮ ግክዳ ተስፋዩ

ሠ. አቶ ይርጋ የሺጥላ

ሬ. ለአቶ ገ/ኮሐንስ እና አስካለማርያም ከነቤተሰባቸው

፫ እርግቴን በሚመለከት ግዕዙን ከአማርኛው ጋር በማስተካከልና ሆሄያትን በመጠበቅ ወርቅ ጊዜያቸውን ለሠውልኝ ለውድ መንድሜ ለቀሲስ ምሕረት ዘውዴ

፬ በሕትመቱ ወቅት ቶሱ እንዲታተም ለረዱኝ ለማተሚያ ቤቱ ኃላፊዎችና ሠራተኞች

፭ እኔህን ታላቅ አባት ያገናኙኝን ደ/ር ይልማ አያሌውና ወ/ሮ ስሎሜ አሰፋን በጠቅላላው በሀሳብ ለረዱኝ ሁሉ ከነ፡ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ከአዘጋጂው

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፅ አምላክ በአብ ስም አምነን አብን ወሳዲ ብለን በወልድ ስም አምነን ወልድን ተወላዲ ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም አምነን መንፈስ ቅዱስን ሠራዒ ብለን ምንም ለአጠይቆ አካላት በስም በማብር በአካል ሦስት ብነል በባሕርይ ቤሕልውና በአገዛዝ በሥልጣን ዘመለከት ሮ ቱን አንድ አምላክ ብለን አምነን ረድኤተ እግዚአብሔርን እጋኝ በማድረግ የነቢየ የባርክን መጽሐፍ መጻፍ እንጀምራለን።

ባርክ ብሂል በሩሳ ዘእግዚአብሔር ባረከ ማለት ነው አባቱ ኔርዩ ይባላል ኔርዩ ማለት ብርሃን ማለት ነው ይህም ባርክ የነቢየ ኤርምያስ ደቀመዝሙር ነው ኤርምያስ የሚዋዋን ነገር ሲናገር እየሰማ ወደ እግዚአብሔር ይለምን ነበር። ልመናውም የኢየሩሳሌምን ልማቷን እንጂ ጥፋቷን አታሳየኝ እያለ ነበር እግዚአብሔርም የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነግ አምላክ ነውና ጥፋቷን በዓይኑ ሳያሳየው ቀርቷል። በቸርነቱ ሠውሮ አድናታል፡ የዳነም እሱ ብቻ አይደለም አስቀድመው ንስሐ የገቡ ሁሉ የኢየሩሳሌምን ጥፋት በጀሯቸው ሰሙ እንጂ በዓይናቸው እንዳያዩ እግዚአብሔር የሰወራቸው ነበሩ ፣ቸው ከዚያም ዘንድ ንጉሡ ኢዮስያስ ፈጣሪዉ የኢየሩሳሌምን ጥፋት አታሳየኝ እያለ ይጸልይ ነበር ጌታም አንተ አስቀድመህ እዝነህ ተከለከ ንስሐ ገብተህ ለምነሃልና እኔ በጥበቤ ሰውርሃለሁ በጀርህ ትሰማለህ እንጂ በዓይንህ አታይም ብሎ ሰውሮ፡ አድናታል።

ዛሬም ጌታ እንደየሥራችን ደስታና መከራ ማፈራረቅ ባሕርዩ እንደሆነ አውቆ የመጽሐፉን ቃል ጠብቆ በሕግ ጸንቶ ሥጋውን ደሙን እየተቀበለ የሚኖር ሰው ሁሉ እግዚአብሔር ከሚያመጣው መከራ ይድናል ወደ ጥንት ነገራችን እንመለስና ይህም ባርክ ሰመምህሩ ኤርምያስ የታመነ የተወደደ አገልጋዩ ነበር ከዚግኑቱም የተነሣ ጌታ ኤርምያስን ይህ ያኛው ሁሉ አይቀርምና ጻፈው አለው ኤርምያስም ለጊዜው ታስሮ ነበርና እየነገረው መጽሐፈ ኤርምያስን የጻፈ እሱ ነው፡

ምዕራፍ ፩

፩. ሪአይ ዘእርእዮ እግዚአብሔር ለቅዱስ ባርክ ወእምድኅረ ኮነ ሱቱ ፲ወ፪ ዓመተ መስድም እዙሁ መእሙ ኢየሩሳሌም መአቀምዉ ቅድመ ሊቀ ካህናት ዘስሙ እለ እስከንድሮስ ወደመሮ ኀበአፃዊ ኃዋኅው።

፩. እግዚአብሔር ለቅዱስ ባርክ የገለጸለት ራእይ ይህ ነው። በተወለደ በ፲፩ዓመቱ እናትና አባቱ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት ወስደው አለእስከነድሮስ ከሚባል ሊቀ ካህናት ፊት አቆሙት አቆሙትም ማለት ለበጎ ነው እንጂ ለክፉ አይደለም ከዘር ጠባቆች ጋር አኖረው ።

፪. ወንበረ እንዘይትለአክ ፳ ዓመተ ወይጼሊ እንዘይብል አታርእየኒ ሙስናሃ ለኢየሩሳሌም ወእምድኅረዝኖ ፳ ዓመተ ወሶረ አቡሚሊክ ከመ ያምጽእ በዳሰ ዘትክሙን ፈውሰ ለአመ-ማን ወእምድኅረ ንሥአ በለሰ ከመ ይሑር ገበ ባርክ ወእንዘ ሀሎ ቤሐዊር ዩከመ አቡሚሊክ ወንብረ ሰረዓኑተ ታሕተ ዕፅ ነዊኅ ወመጽአ ሳሰሌሁ ንዋም ወኖመ ፸፮ ወሀ ዘዩቢ ሮጊ ዓመተ ወእምድኅረ ዝንቱ ተራክዘ ምስለ እንዘሁ ባርክ ወነበሩ ኅቡረ እምቅድመ ሚጠተ እስራኤል ፲ወ፭ ዓመተ።

፫. ከእነሱ ጋር እያገለገለ ፹ ዓመት ተቀመጠ አገልግሎቱም የኢየሩሳሌምን ጥፋቷን አታሳየኝ እያለ ይጸልይ ነበር። ዘወትር እግዚአብሔርን በጸሎት ማሰብ እግዚአብሔርን ማገልገል ነውና ፹ ዓመት ከሆነው በኋላ አቡሚሊክ ለሕመማን ፈውስ የምትሆን ዕፀ በለስን ያመጣ ዘንድ ወደ በረሀ ሄደ በለሊቱን ቀጥፎ ይዞ ሲመለስ ደክሞት በታላቅ ዛፍ ሥር አረፈ። በዚያም ሳለ እንቅልፍ እንቅልፍ አለውና ፸፮ ዘመን ተኛ ከዚህ በኋላ ከእንቅልፉ ተነሥቶ ወደ ወንድሙ ወደ ባርክ ሄደ። ከእስራኤል ምርኮ መመለስ በፊት ፲፩ ዓመታት አብረው ተቀመጡ ይኸውም የበለስ ቅጠል ሰፊ ነው ኃጢአት በዓለም ሰፍና ትኖራለች ሲል ነው የበለስ ቅጠል ሲበሉት ይጉመዠዠል ኃጢአትም ሲሠሩት ደስ ይላል እንጂ በኋላ ያሳዝናል ከዚህ በኋላ እንቅልፍ መጥቶበት "ሟች" "ሟች" ዘመን ተኛ ይኸውም ለመረመረው ሰው የእግዚአብሔር ቸርነት ሰፊነው ሰፊነቱም በዚህ ይታወቃል መልአክ ያይደለ እሩቅ ብእሲ ማሰት ሥጋ የለበሰ ሰው ይህን ያህል ዘመን እህል ውኃ ሳይቀምስ ሌትና መዓልት ሳይለይ መኖር ጉዳት ሳይኖርበት ይህን ያህል ዘመን በእንቅልፍ ማሳለፍ ምን ይረቅ ምን ይደንቅ ጊታ ለወዳጆቹ የሚያደርገው ቸርነት ዕጹብ ድንቅ ነውና ወሰን የለውም።

፬. ወእንሥአ እግዚአብሔር ለናቡከደናጾር ንጉሠ ፋርስ በመዋዕለ፡ሁ ለምናሴ ንጉሠ እስራኤል ሄወዋ ለኢየሩሳሌም ወእጥፍአ ኵሉ
ልሕኵታቲሃ ወሄወዋ ለጽዮን ወእማሰነ እሕጉሪሃ ለኢየሩሳሌም
ወነሥአ ወርቀ እምሕንጻሃ ለጽዮን ወነሥአ ያክንተ ወዕንቍ

ባሕርይ ዘእግረ ሰሎሞን ወሄወዉ ሰብአ ወእንስሳ።

፭. ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሊያጠፋም ሊያለማም በፍጡር አድር ነውና የፋርስ ንጉሥ ናቡከደናጾርን
በእስራኤል ንጉሥ በምናሴ ዘመን ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው በኢየሩሳሌም ምርኮ ጊዜ ሰሎሞን ያሠራውን ገንቦውን ወርቁን ነሥ ሐሩን ዕንቍን ከተማውን ገጠሩን ሁሉ ማርኮ አጠፋ ሀገሪቱንም እጅ አደረገ ።

፮. ወመጽአ ዓቢይ መልአክ ሱቱኤል ወነሥአ ለባርክ ወአዕረገ ለማያት ወአርአዮ ኵሎ ዘነበሰ ወዘነበሩት ወአብአ ውስተ ኢየሩሳሌም ለማያዊት ወአርአዮ መናብርተ ልዑላተ ውማንደራቲ ሥርግዋቱ ወአክሊላተ ብሩሃተ ዘዘዚአሁ ራእዮሙ ወአልባሳተ ጽዕድዋተ ዘዘዚአሁ አምሳሊሆሙ።

፯. ሰውንም ከብቱንም ማረከ ከዚህ በኋላ ደገኛ መልአክ ሱቱኤል መጣ ባርክን ይዞ ወደ ለማይ አወጣው አውጥቶም የተሠወረውንም የተገለጸውንም አሳየው ቀጥሎ ወደ ለማያዊት ኢየሩሳሌም አስገባው ለማያዊት አላት ልዕልናዋን ሲያይ ነው መልካቸው ልዩ ልዩ የሚሆን ጉራስ እየራሳቸው የተዘጋጁ ዙፋኖችን የተጌጹ የተሸለሙ አዳራሾችን ብሩሃት የሆኑ አክሊሎችን የወርቅ ዘውዶችን አሳየው መልካቸው ጎበራቸው ልዩ ልዩ የሆነ የተጌጹ ንጹሐት የሆኑ አልባሳትን አሳየው።

፰፣ ወተስእልዎ፡ሥ አነ ባርክ ለውእቱ መልአክ ዘያመርሐኒ ወአቤሎ ዝማንሂር ለመኑ ዘአውሥአኒ ወይቤለኒ ዝማንሂር ለለማዕታት አለመነንሥ ለዝንቱ ዓለም ኃላፊ አለመጠጪ ነፍሶሙ ለሞት በአንተጽድት ወሕይወት አለተመትሩ ርእሶሙ ወከዐው ደሞሙ።

፱. ያን የሚመራኝ ባልደረባዬ መልአኩን እንዲህ አልሁት ያሳየኸኝ በታምኖች ለማን ይሆናሉ አልሁት፡ መለሰልኝ እንዲህም አለኝ ይህ ቦታ ይህን ዓለም ንቀው አታለው የወዲያኖውን ዓለም መርጠው ኃላፊውን ዓለም በማያልፈው ዓለም ለውጠው ሰውነታቸውን ሌሎችም ለሞት ለጥተው አሳቱን ስለቱን ታግሰው ደማቸውን አፍሰው መንግሥተ ለማያትን ወርሰው ከፀሐይ ጌት እጅ አብርተው በዚህ ሁሉ መከራ ፈጣሪያቸውን መስለው የሚኖሩ የለማዕታት ነው አለኝ።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

፮. ወአምዝ አርአየኒ አንጻረሃ ለአቦሃ ሳሉም ሰማዕዊት ዘይውኀዝ ባሕር ፈለገ መዓር።

፮. ዝ ሊናገረው የመጣ ነው ከዚህ ቀጥሎ በኢየሩሳሌም አንጻር ፊት ለፊት መዓር የሚፈስበት ወንዝ አሳየኝ።

፮ ውተስእልክሥ ለዘይመርሐኒ ወእዜሉ እለመን ሊቃውሩ ውስቴቱ ለዝ ፈለግ።

፮. የሚመራኝ ባልደረባዬ መልአኩን ጠየቅሁት እንዲህ አልሁት፡ በዚህ ወንዝ ውስጥ የሚኖሩ ማለት ከዚህ ገብተው የሚኖሩ እነማን ናቸው አልሁት።።
፮ ወአውሥአኒ ወይዜለኒ ለክቢያት እለ ተነበዩ በእንተ ክርስቶስ።

፰. መለስልኝ እንዲህም አለኝ። ስለ ክርስቶስ ትንቢት የተናገሩ ማለት ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት የሚሆነውን የሚናገሩ የክቢያት፣ ክርስቶስ ያስተማረውን ያስተማሩ ሥጋዌውን ሕማሙን ሞቱን ትንሣኤውን ዕርገቱን ዳግም ምጽአቱን ሊያስተምሩ የኖሩ ሐዋርያት ቦታ ነው አለኝ።

፰. ወአምድኅረዝ አርአየኒ አንጻረሁ ለውኅቱ ፈለግ ፈለገ ወይን ዘይውኀዝ ከመማየ ባሕር።

፰. ከዚህ ቀጥሎ በዚህ ወንዝ አፋዛኝ (በዚህ አንጻር) እንደ ፈላሽ ውኃ ወይም እንደ ባሕር ያለ ወይን ያለበት ወንዝ አሳየኝ።

፮. ውተስዕልክሥ ለዘይመርሐኒ ወእዜሉ እለመነ ዘይበውኡ ውስ ዝንቱ ፈለግ ወይቤለኒ አለመነንሥ ለዝንቱ ዓለም ኃላፊ መፍቀርያ ነገድ ወእለያፈቅሩ ቢጸሙ ከመነፍሶሙ ::

፮. የሚመራኝ ባልደረባዬ መልአኩን ጠየቀሁት አንዲህ አልሁት ወደዚህ ወንዝ ገብተው የሚኖሩ እነማን ናቸው አልሁት ኃላፊውን ዓለም በማያልፈው ዓለም ለውጠው በሃይማኖት ጸንተው በምናኔ የሚኖሩ እንግዳ የሚቀበሉ ባልንጀራቸውን እንደራሳቸው አድርገው ለሚወዱ ለሰች ነው አለኝ።

፱. ወአምዝ መርሐኒ ወዕበየኒ ኀበ ዓምደ ወርቅ መንክለ ምሥራቅ በጽሑፍ ውስቴቱ ዘይቀትቱ ጽሑፈቱ ዘያዘርህ እምፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብት ውስተ ወስአልክሥ ወእዜሉ ምንት ውስቴ ዝኅምጸወርቅ።

፲፩. ከዚህ ቀጥሎ በምሥራቅ በኩል የወርቅ ምሰሶ ቁዳለበት ወሰደኝ በዚህም የወርቅ ምሰሶ ላይ ከፀሐይ ከጨረቃ ከከዋክብት ይልቅ የሚያበራ ረቂቅ ጹሑፍ፡ ተጽፎበታል ይህ ረቂቅ ጽሑፍ የተጻፈበት የወርቅ ምሰሶ ምንድነው ብዬ ጠየቅሁት ::

፱. ወአውሥአኒ ወይዜለኒ አስማተ ሠለስቱ ዘአጽዕቆን ለዝ ዓምደ ወርቅ ኀበ እደ፡ ወእደ ማስን ወሥሉተ ሕይወት ወእዜሉ ዘነሕቲቶሙኑ ተጽሕፈ ውሚመ መለአነኅ ኮ፦ሉ፦ መ፦ አጽዕቆን ዘዝ ዓምደ ወርቅ ውስተ ሕይወት ኀበአያበለ. ወእይማስን ወእዜሉ እምአጽምኑ ወይዜለኒ እምአጽም እስከንልቀቱ ዓለም ጽሑፍ አስማተ፡ሆመ ለጸድቃን በዝ ዓምደ ወርቅ።

፲፪. ጎልፈት ጥፍአት በሌለበት በሕይወት የሚኖሩ የጻድቃን ስማቸው የተጻፈበት ነው አለኝ፡ በዚህ ዓምደ ወርቅ ላይ የተጻፈ የእነርሱ ስም ብቻ ነውን "አልሁት" ወይስ እነርሱን የመሰሉ የጻድቃን ስም ነው ወይስ ከአዳም ጀምሮ ነውን አልሁት፡ አም ከአዳም ጀምሮ እስከ ጎልቀተ ዓለም የሚነሱ ጻድቃን ስማቸው በዚህ ዓምደ ወርቅ ተጽፏል አለኝ።

፲፫፣ ወእምዝ አብአኒ ውሳጥያተሃ ለይሕቲ ዓምድ ወርኢኩ በህየ መናብርተ ዓበይተ ሐዋርያት ወአክሊሎተ ብሩሃተ ወአልባሰ ዕፅድዋተ ዘይዐውድው እምባሕሩ ዘከመርኅ ወከዋክብት ወምሉዕ ውስቴቱ ፍሬያተ።

፲፫. ከዚህ በኋላ ወደዚያች ምሰሶ ውስጥ አገባኝ ማለት የወርቅ ምሰሶ ወዳለበት አገባኝ፡ በዚያ የሚያበሩ የወርቅ ዘውዶች ደጋጮች ዙፋኖችን አየሁ፡ ከፀሐይ ከጨረቃ ከከዋክብት ይልቅ የሚያበሩ ልብሶችንም አየሁ በውስጡም ፍሬን ተሞልቷል አለ የጻድቃን ክብራቸው ነው።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

፲፬. የሚመራኝ ባልደረባዬ መልእክቱን ጠየቅሁት እንዲህ አልሁት ወደሷ የሚሸ እንግዳ ናቸው አልሁት መልሶ እንዲህ አለኝ በዚህ ዘመንገሥተሰማያት በር የሚጠሩ የሚሸ ባል በሚስቱ ሚስት በባሏ ጸንተው የሚኖሩ ናቸው አለኝ: የወርቅ ዙፋኖች የሰንፋ ምኳኳፍች የጠርቅ መከዳ ትራስ የተሰጣቸው ናቸው አለኝ የሚመራኝ ባልደረባዬ መልእክቱን እንዲህ አልሁት እነዚህስ እንድ የሆኑ ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ነውን ብዬ ጠየቅሁት እም እርሱም ከእርሷ በቀር እርሷም ከእርሱ በቀር ሴላ እያውቁም አለኝ::

፲፭. ወእምዝ ወሰደኒ ወነሥአኒ ወአብጽሐኒ ኀበይእቲ ሀገር ወርእኩ በዛሞ ብዙኃ አትክልተ ኅሶልፍ ያማወጀቱ ወምሱዕ ውስቱቱ ፍሬያተ::

፲፮. ዝ ከዚህ ቀጥሎ ወደዚያች ሀገር ወሰደኝ በዚያም ኅሶልፍ ያማወጀ አትክልቶችን አየሁ ብዙ ፍሬን የተሞሉ ናቸው::

፲፯. ውስጠልልከም ለዘያመርሐኒ ወእቤሉ አለመኑ ያብሠሉ ውስቲታ አውሥእኒ ወደዜለኒ እለጸልዕም ወመነንም ለዝንቱ ዓለም ኃላፊ ወዝንቱ አንቀጽ ዘንበረ ውስቲቱ አዳም ወይእዜኒ ይሴፈውም ብዙኃን ወይብውዕም ውኁዳን ::

፲፰. የሚመራኝ ባልደረባዬ መልእክቱን እንዲህ አልሁት ወደውስጧ የሚሸ እንግዳ ናቸው አልሁት:መልሶ እንዲህ አለኝ ይህን ኃላፊ ዓለም ሹመቱን ሽልማቱን ተድላ ደስታውን ንቀው በጾም በጸሎት ተወስነው የሚኖሩ ናቸው አለኝ: ይህም አንቀጽ የተባለው ተድሞ አዳም እየወጣ እየገባ የኖረበት ገነት ነው: ይህንንም ተሰፋ አለኝታ ሊያደርጉ ናረው የሚሸበት ጸድቃን ጥቂቶች ናቸው አለኝ ::

፲፱. ወእምዝ ወሰደኒ ወአብጽሐኒ ኀበሀገረ ቅብዕ ወእቤሉ ለዘያመርሐኒ እለመኑ ይብውኩ ውስተ ዝንቱ አንቀጽ::

፳ ከዚህ ቀጥሎ ቅቤ ወዳሰበት ሀገር ወሰደኝ አለ ፍቅር አንድነት ጸጋ ኩብር ወዳሰበት ወሰደኝ የሚመራኝ ባልደረባዬ መልእክቱን እንዲህ አልሁት: ወደዚህ የሚሸ እንግዳ ናቸው አልሁት::

፳፩. ወይቤለኒ እለጸልዕም ለዘንቱ ኅሶልም ወመነንም አስኩተናጺጣተ መዋለለሆሙ: ወእምድኅረ ነሥኡ አክሊለ ንጽሕተ ወተሐርሙ በንጹሕ ልብ ሥጋ ወነፍሰ::

፳፪. ይህን ዓለም ከተፈጠሩ ይምሮ እሰከሰተ ሞታቸው ማለት ከዚህ ዓለም በሞት እስኪለዩ ድረስ ተድላ ደስታውን ንቀው የኖሩ ናቸው አለኝ ከመነኮሱ በኋላ ምንኩስናቸውን ሳያሳድፉ በዝሙት ሳይሰነካከሱ ሥጋ ሳይበሱ ወተት ሳይጠጡ ከቂም ከበቀል ንጹሕ በሆነ ልቡና ጸንተው የሚኖሩ ናቸው:አለኝ::

፳፫. መእምዝ ወሰደኒ መአብጽሐኒ አንጻረሙ ለመንቱ ፈለግ ፈለግ ሐሊብ እንዘ ውስቱ ይፈደፍድ እምውስቱ ፈለግ እምባሕር መእምቀላያት መእቤሉ ለዘሂመርሐኒ አስመኑ ይብውኩ ወየኃድሩ ውስተዝ ፈለግ::

፳፬. ከዚህ በኋላ በዚያ ወንዝ እንጻር ወዳለ ከባሕር ከፈላሽ ውኃ የሚበዛ የውተት ወንዝ ወዳለበት ወሰደኝ የሚመራኝ ባልደረባዬ መልእክቱን እንዲህ አልሁት ወደዚህ ወንዝ ገብተው የሚኖሩ እንግን ናቸው አልሁት ::

፳፭. ወይቤለኒ ሕጻናት እለ ኀርሩ እምከርሠ እሞሙ ወበደኃሪ መዋዕል ያጸልሉ: እሙያ ከብሳኖ ክርስቶስ እለ ተቀትሉ ሕጻናት ፲ወ፬ዕልፍ ወሣሪ አሙነ፣ ያጸልሉ ውስተ ፈለግ ዓዚያ ወእኩ ለሕጻናት ባሕቲቶሙ እሳ መነኮሳት እለጸልዕም ወመነንም ለዝንቱ ዓለም ኃላፊ ወእለተሐርሩ እምዝሥሥ እሞሙ ለመንገሥተ ሰማያት ወእምከመነፆኡ እስኪማ ንጽሕተ እለኢተደመሩ ምስለ አንስት ወእሙንቱሂ ያጸልሉ ምስለ ሕጻናት::

፳፮. ከናታቸው ማነፀን ጀምሮ የተመረጡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ሄሮደስ ያስፈጃቸው ፲ወእልፍ ከፀሺ ሰማዕታት ሕጻናት በዚህ በወተቱ ወንዝ ተጠግተው ይኖራሉ ማለት ርስታቸው እድርገው በኋላ ዘመን ይኖሩበታል አለኝ:

ይኸውም ቦታ ለሕጻናት ብቻ አይደለም ይህን ዓለም የናቁ ያቃለሉ ማለት የዚህን ዓለም ተድላ ደስ ንቀው አቃለው የሚኖሩ ከናታቸው ማሕፀን ጀምሮ ለመንገሥተ ሰማያት የተመረጡ ከመነኮሱ በኋላ ከሴት ጋር

Scanned by DocumentScanner | Lufick

እንድ ያልሆኑ ማለት ከሌት ጋር ተኝተው ንጽሕናቸውን ያላላደፉ መዝሙሳት ከዝህ ሕፃናት ጋር ይናሩበታል እንጂ።

ምዕራፍ ፪

፩. መእምዝ መሰደኒ መአብጽሐኒ ውስተ ሀገር ጽዕዱት ወሥርጉት በውርቅ መሀሰከት ወዛዕንሎ ባሕረይ ወምሉሰ ውስቲታ ፋራያት አትክልት ለውዝ ንውዝ ውብዙኃት አትክልት ተምር መእው ያን ወሮማን ወተክለልክም ለዘይመርሐኒ መእዜሉ። እሰመን ያዜሙስ ውስተ ዝማንደር።

፩. ዝ ሊናገረው የመጣ ነው በውርቅ በንጭ ሐር በሰንቋ የታነጸች የተቀደረች ጽድልት (ሻልምልም) ብርህት ወደምትሆን ሀገር ወሰደኝ በውስጧም ለውዝ፡ንውዝ፡ተምር፡ ወይን ፡ሮማን አሰጣት። የሚመራኝ ባልደረባዬ መልአኩን እንዲህ አልሁት ወደዚህ የሚዝኑ እንማናናቸው አልሁት።

፪ ወደልዕኒ ሰንሥት ወለመኳንንት አለየአቅቡ ፍትሐ መአሰ ኢያደለጢ ለገጽ ኢለነዐል ወኢለንዳይ መአለ ያፈቅሩ እንሰማውታ ወሰቢራ ተ ብአለ ያፈቅሩ ካፍናተ መአለያሠረገጫ አብያተክርስቲያናተ በአልባበ ተብንት መአለያፈቅሩ መዝሙሳተ ውመበለታተ መአለያሐቡ ምጸዋተ ለነዳያን መሰአንለማውታ መአለያበልኡ ሰርሁነን እምኀብስተ ወአለያስተየ ለጀሙአን እምጽዋአሙ መአለያለብሱ ሰዕሩቃን እምልብሰው ዝንቱ ወአቱ ማንደርሙ፡ ለአሙንቱ ነገሥት።

፪. ፍርድ ሰሚጠፍቁ ማለት ፍርድ ለማያደሉ መማለጃ ለማይቀበሉ ፊተ አደተው ለማያደሉ ለሀሰሰፀጋም ቢሆን ለድኃም ቢሆን ማለተ ባሰሰፀ.ጋ ነውና ልፍረድበት ድኃነውና ልፍረድበት ለማይሉ እናተ አባቱ የሞቱበትን ባልቴቲን ሰሚረዱ ካህናትን ለማያከብሩ አብያተ ቤተክርስተያናትን ያልተመራውን እየሠሩ የፈረሰውን እያደሱ ለሚያከብሩ መነኮሳቱን ይሆናን ሰሚረዱ ለሚወዱ እዝህን ለመሰለ ሁሉ ምጽዋት ለማሰጠ ከማዘበሉት ከፍለው ለተራብ ለሚያበሱ ለተጠማ ለሚያጠጡ ለታረዘ ለማያለብሱ ለነገሥታት ለመኳንንት ቦታቸው መኖሪያቸው ይህ ነው አለኝ።

፫. መእምዝ መሰደኒ አንጸረሁ ሰውአቱ ማኅደር መአሰረገኒ በሐመረ መርቅ መአብጽሐኒ ኀበሀገረ ክርስቶስ መአርአየኒ ክብረ ነገሥታት ዘኢየኃልፍ በበተሰልፈት ሰልፍ ይሰህቅ ወይክብር። መእዜሉ ለዘይመርሐኒ ምንተ ሰሙ ሰ ዘ ሀገር።

፫. ከዚህ ቀጥሎ በዘህ ቦታ አንጻር ወዳለ ሀገረ ክርስቶስ ወደሚባል በወርቅ መርከብ አስቀምጦ መሰደኝ የማያልፍ የነገሥታቱን ክብር ከአልፍ አእላፋት የማልቅ ማለት የሚበዛ ከሁሉ የሚከብር የነገሥታቱን ክብር አሳየኝ፡ የሚመራኝ ባልደረባዬ መልአኩን እንዲህ አልሁት የዘህ ሀገር ሰሙ ምንድነው ማለት ማን ይባላል አልሁት።

፬. ወይቤለኒ ሀገረ እግዚአብሔር ሀገረ ክርስቶስ ሀገረመንፈስ ቅዱስ፡መአቤሉ አሰመኑ ያህሀሎአ ውስተ ዝሀገር ወአውሥአኒ ዘያመርሐኒ፡ ወይቤለኒ፡ የሞሃን ሰለኢያአኅዙ ቁመ ውስተ ልቦሙ ወአለያገብሩ ስላመ ምስሶ ቢጹሙ ወአለ ይፈድይም ሠናየ ለዘገብረሉ-ሙ እዚተ ሩአሰይሠርክሠ ለዘረገሞሙ መአለ አብልሰም ለርሁብ እምሲሳየ-ሙ ወአለ አብተ ይም ለጽሙዕ እምስቲሆ-ሙ ወያለብስም ሰራ ት እምልብሰሙ ወይትቤዘውሥ ለግፉዕ በንዛየ-ሙ መአሰያሰትሕሠ ለንዳይ እምወርቆሙ ዝኬ ውስቱ ማንደሮሙ ለየሞኑን ።

፭፡ እንድ ወገን ነው የባሕርይ አባቱ የአብ የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ ሕይወቱ የመንፈስ ቅዱስ ሀገር ነው አለኝ። ወደዚህ ሀገር የሚዝኑ እንማን ናቸው አልሁት። የሚመራኝ መልአክ መሰሰልኝ እንዲህ አለኝ። በልቡናቸው ቂም በቀል የማይዙ ከንጽሐ ጠባይ የደረሱ ከባልጀራቸው ጋር ፍቅር አንድነትን የሚያደርጉ ክፉ ላደረገባቸው በጉ የሚያደርጉ የማረገሚቸውን የሚመርቁ ለተራበው ከምግባቸው ከፍለው የሚሰጡ የሚያጠግቡ ለተጠማው ከሚጠጡት ከፍለው የሚያጠጡ ለታረዘ የሚያለብሱ የተበደለውን ከገንዘባቸው ሰጥተው የሚቤገ ማለት የማረዱ ከገንዘባቸው ለድኃ አበድረው አራጣ ማለት ወለድ የማይቀበሉ ቅን ልቡና ትሑት ሰብእና ሳላቸው የደጋግ ሰዎች ቦታቸው መኖሪያቸው ይህ ነው አለኝ።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ትጠል አለባት ይኸውም የጣፈጠ ነው እንጂ የመረረ የጉመዘዘ አይደለም ሽታዋም ከጣዕሙ ብዛት የተነሣ ልብ ይመስጣል ይልቁንም ከጣዕሙ ብዛት የተነሣ ነፍስ ከሥጋ ይለያል፡ ነገር ግን መጀመሪያውም መጪረሻውም አይታወቅም ከአብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ቡዞ የሚያውቃት የለም መላእክትም አያውቋትም ካህናትም አያዋኗትም።

፲፭. ውተክዕልዚሙ ወእቤሉ አለመኑ ይብሎሙ ውስተ ዝማንየ ወይቤለኒ መነኮሳት።

፲፮. ባልደረባዬ መልእኩን ጠየኩት ወደዚህ ቦታ የሚገቡ አነማን ናቸው አልሁት መነኮሳት ናቸው አለኝ።

፲፯. ወእቤሉ ኩሉሙት መነኮሳት ይብሎሁ ውስተ ዝ ማንየ ወይቤለኒ አልቦ ወእቤሉ አለመኑ ይብሎሉ ወይቤለኒ እምአመ ነሥአ አስኬማ ንጽሕተ እለኪተደመሩ ምስለ እንስት ወእለኪያቶሰ ቢጸሙ ይጸልናሙ ወእለ ኢያጽሩ መነብርተ ዓበይቶ መዘኢነበሩ ሠናይቱ ወመኢያትረደ ወርቀ ውዑረ

ዓለም ኃላፊ መዘኢያፍቀሩ ሚመተ ወኢሰከሙ ውስተንፃረ ሰመንእፃት መዘኢያመክዝ ለዕሊይ ወለከተይ እንዘይብሉ በነፍስ ሞም ወነፍስነመ በሣል ለመነኮሳት ይዲብ ምድር ወፋሲክየሙ እስከ ጸአተ ንፍሶሙ እምዝ ዓለም ኃላፊ ወእለኢያፍቀሩ ተወድሶ ክንቱ ወዘኢንሥኡ ወርቃ ውዑረ እምጋብ ነገሥት ወመኢንንት ወዘኢያንበሩ አክሊለ ዳብርእሶሙ ወዘኢይነሥኡ ሠልጦ ወሳዕለ ንጹሕ እሙንቱ እለ ይብሎሁ ውስተ ዝንቱ ማኅደር።

፲፰. ወደዚህ ቦታ የሚገቡ መነኮሳት ሁሉ ናቸውን ብዬ ጠየኩት አይደሉም እሊህ ያልገቡ የሚገቡ እንግን ናቸው አልሁት ከመነኮሱ በኋላ ክሌት ጋር ያልተኙ ነገር እየሠሩ ባልጀራቸውን ያላስገደሉ ደጋግ ዙፋን አሠርተው በዚያ ያልተቀመጡ ወርቅ ብር ያላጠራቀሙ ይህን ዓለም ንቀው መንነው ሹመት የማይወዱ ከዙፋን ከወላንላ ምንጣፍ ላይ ተኝተው ደስ ያልተሰኙ ዛሬ በኋል ነው እያሉ ለመብላት ለመጠጣት ምክንያት የማይሰጡ ግለት በክብረ በዓል ምክንያት የማይበሉ የማይጠጡ ናቸው አለኝ እንዲህም ማለቱ በዚህ ዓለም

ለመነኮሳት በኋል የሳቸውም የእነርሱ ደስታቸው ፋሲካቸው ነፍሳቸው ከስጋቸው እስኪለይ ድረስ ትሩፋት መሥራት ነው በዚህ ውሚያልፈው ዓለም ከንቱ የሆነ ውዳሴ ከንቱ የማይወዱ ከነገሥታቱ ከመኳንቱ ወርቅ ብር የማይቀበሉ በራሳቸው ዘውድ የማይደፉ ማለት ምድራዊ ክብርን የማይወዱ ከንጹሕ ከድህው መማለጃ የማይቀበሉ በዚህ ቦታ ገብተው የሚኖሩ እሊህ ናቸው አለኝ።

፲፱. ወአመ ሰዐልኩ አእኩትክሙ ወሰባሕክሙ ለእግዚአብሔር።

፲፱. ከዚህ በኋላ ፈጽሜ እግዚአብሔርን አመሰገንኩት።

ምዕራፍ ፫

፩. ወእምዝ ወሰደኒ ምዕራብ ወበህየ ርኢኩ ዓምደ እሳት ዘጽሑፍ በቀለመ እሳት ወደቃቅ ጽሕፈቱ ወጽፋቅ ዘይበዝኀ እምአዕማድ ዘወርቅ።

፪. ከዚህ ቀጥሎ ወደ ምዕራብ ወሰደኝ በዚያም ቦታ በእሳት ቀለም የተጻፈበት የእሳት ምሰሶ አየሁ ጽሕፈቱም እጅግ ደቃቅ ነው ይኸውም ከወርቅ አዕማድ የሚበዛ ንብብር ቅጥልጥል ነው።

፫. ወተሰፈወኩክሙ ወእቤሉ አለመኑ እለጸሑፉን ውስተዝ ዓምደ እሳት ወይቤለኒ አስማ ኮሎሙ ሰንጥአን ወርኢኩ አንጻሪሁ ደናግል እንዘያሰብሳ ጽልመተ ወእቤሉ አሳንቱ አለመኑ ወይቤለኒ ደናግል አብዳት እሱራን ዕድ ወእቤሉ በእንተ እደዊሆንኑ ይቀውማ ውስተ ዝንቱ ወይቤለኒ እወ።

፬. በዚህ በእሳት ምሰሶ ላይ የተጻፉ እንግን ናቸው ብዬ ጠየኩት አስማተ ኃጥአን ናቸው ማለት ስማቸው በእሳት ምሰሶ ላይ የተጻፈ ኃጥአን ናቸው በዚያ አንግር ጨለማን የተጉናፀፉ ደናግልን አየሁ እሊህ እንግን ናቸው አልኩት እጃቸው የታሰረ ሰነፎች ማለት በጉ ሥራ የማይሠሩ ደናግል ናቸው አለኝ በዚህ የቆሙ የፀኑ በልቦናቸው ስንፍና ይሆን አልኩት አም በልቡናቸው ድንቁርና ስንፍና ነው አለኝ።

፭. ወድኅሬሁ ርኢኩ ፈለገ እሳት ዘምሰዕ ውስቴቱ ሰብ ብዙኅ ወያነብርሥሙ ዲበ አትሮንስ እሳት ውተስእልክሙ (ለውእቱ መልአክ) ወእቤሉ ለዘያመርሐኒ እሉ እለመኑ ዘመጠነዝ ኩነኔ ሆሙ ወይቤለኒ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

፩. ወአውጽእኒ እምውስቴቱ ማኅደር ወአንቀጽ መጠባደኒ ንስኪልዕት ሠገር እንተነግግ አትራፃ ዘይብልዎ ዜሐረ ሕያዋን። አውጽአኒ መጠባደኒ መጠቦ ርኢክሙ ለጊናክ ወለአልያስ እንዘይጽሕፉ ምክራ-ቲሆሙ ለደቂቃን በቁርባ ወረት መጠቦ ሰሎሞን ሊቀ ካህናት በቁርባ ፌጊን መጠቦት። ወተነበልክሙ ወአበሉ ለዘይመርሐኒ አለመኑ ይሕተ ሥጋ ወአመነት አሉ አለይደሕቱ።

፪. እንድ ሠገን ነው ክዚያ አውጥኖ ክዚያ ወር አውጥኖ አትራፃ መደምትባል ሠገር መጠገን ይጌውዖ ዜሐረ አያዋን ትቁልቶት።ወዚያም ሄናክና ኤልያስን የጊድያን ሥራቸውን ክመርቅ ወር የኃጣንን ሥራ ሃን በዓረት ብሉር ለደቡ አየገቸው። የሚመሩኝ ዜአየረዜ መልአኩን እንዲህ አልሁት። ይህቺ አገር የማን ናት ይሰንክ የሚደቡ አያዋን ናቸው ብዜ መጠቡት።

፫. መጠባደኒ ዛተ ሠገር ዜሐረ አያዋን ይሕቲ መአሩቲ ሄናክ መአሊያስ አይደክሙ ትክክ ዜአገዜአቸውና መአሊያክሙ ለንአሙ።

፬. ይህቺ አገር ዜሐረ አያዋን ናት አዜሙ ለምቾ ሄናክና አሊያስ ናቸው ወአገዜአቸውን ትወዝ የሚደቡ ክመንግሥ ጸንተው የሚናሩ ናቸው አዜ።

፭. መጠባደኒ መጠቦን ንስኪልዕት ሠገር። ወርአኑ ውስተ አናቅጺሃ ሰፊ ዛጊ ወማክ ናፊ መጠቡትቲ ክርዋን ውስተቱ። ወማዚያ ረጋዕ ይርገው መጠጋው መአደግ ወው ዋተ ወአቱ ሰፎ የንርት (ወየንርት) ውስተ ይግደት መጠመጠ ለዕዜ ይጠቡ ዜናክ ወውስተ ሰማይ ይወርዱ ውስተ ምድር መወሰቱ ለደን ክዜ ለዕዜ ይሕተቱ ይትገዛ ውስተ ምድር ወውስተ የመርገም ስዘንተመዘ ወየንተርሰሙ ወክዜ ተሰወዜክም ሰውስቱ ምድር ወክዜ ዜመርሐኒ ወክዜው አገዜ አገዜን ዜሐሙት ዝግገር።

፮. ክዚያ አውጥኖ ወር ክለ አገር ወጠገን ወዚያችም ወር ፍሬን የተመጣ ታክት ክለ አየው ወውስጣም መጠሩት ተፀትነየል ግክት አሉ ጽኑ ረወዘ ይሕው ይጠጡ ዜገር ክወዮ አመገዜ ወገን ክለ እንዚህም መነሱሳት ወደ ቅግዚ ይወጣ ወደአግዜ ክወው ደክለ ዜገው (ዜወርዱ) ይወዱ ወደ ምድር ደወርው እንዚህም ግክት ፀተረፕርክተው ምድራውያን ሲሆኑ የማዜንቱ ምግዜውያን ናቸው ሰግዜውያን ክመኑ ወንክም በኃጣአታቸው ይተሃክ። ያም ወገዜ ዜወጡ ክወደዱ ጊዜ ወደ ምድር ንፁተ ይሰወራቸየል መጠጣትን ፀተወትም ጊዜ ተገዜኔ ይታያየየል የሚመራኝን መልአክ ይህ ዖታ ዜሆን ነው ወጹ መየትሁት።

፯፡ ወአውሥአኒ ወይቤለኒ ዝከሃር ለመነኰሳት በየግዚ ፍጹማን ወወጸሎትዚ ፍጹማን ወዘንጸሐ ሥጋዚ ፍጹማን ወባሁቱ አኮ ዝጥራን ወሰዙያን።

፰. ይህ አገር ለመነኰሳት ነው ይኸውም በትሩፋት ፍፁማን፣ በጸሎትም ፍጹማን፣ በንጽሐ ሥጋ ፍጹማን ለሆኑ ነው እንጂ ለተዕቢተኞችና ለተዝናርተኞች (ለጉረኞች) አይደለም።

፱. አውሣእክም ወአቤሎ ትዝናርቶሙኑ ከልአሙ በዚአ ውስተመንግሥተ ሰማያት፡ ወይቤለኒ ሥርዋ ለኃጢአት ትዝናርት ወትዕቢት።

፲. ወደመንግሥተ ሰማያት ከመግባት የከለከላቸው ትዕቢታቸው ነው ወይስ ትዝናርታቸው (ጉራቸው) ነው ብዬ ጠየቅሁት መልአኩም መለሰልኝ እንዲህ አለኝ የኃጢአት መገኛዋ ሥር መሠረቷ ትዕቢትና ትዝናርት (ጉራ) ናቸው አለኝ።

፲፩. ወለምዝ እርእየኒ ሀገረ ብርሀተ ትዕልፊተ አእላፋት እምፀሐይ ወወርኀ ወክዋክብት ወምልዕት ፍሬ ለሰሰዓቱ በዘምዕት ይፈሪ ወምልዕት ፍሬ በረከት ወአልባስሂ ብሩሃተ ዓበይተ ወአክሊላቲ ወቅናተ ዘወርቅ ወክኖናተሂ ዘዕንቊ ባሕርይ ወመንጸፍኒ ዘቆጸናት በየግና ወበፀጋግ አዕውቀ ዘይት ሥሙር ወዒና መዓዛሃ ዘይሐልቁ ልበ እምብዝኀ ጣዕሙ ፈድፋደ ያወጽአ ነፍሰ አምሥጋሃ ወኢይትአወቅ ጥንቱ ወኢተፍጻሜቱ ወአልቦ ዘየአምራ ዘአንበለ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወመላእክትኒ ኢየአምርዋ ወክህናትኒ ኢየአጥንዋ ።

፲፪. ከዚህ ቀጥሎ ብርሀት አገር አሳየኝ አለ ከፀሐይ ከጨረቃ ከክዋክብት ረጅግ የምታበራ አገር አሳየኝ በየጊዜው በየ ሰዓቱ አልፍ አልፍ ፍሬ ታፈራለች ፍሬ በረከትን የተሞላች ናት ልብሶቿም ብሩህት የሆኑ ደጋግ ናቸው የወርቅ አክሊል የወርቅ ዝናር የዕንቊ መጦናጸፊያ ቆጸን (ህብረ ብዙ) የሚባል ምንጣፍ አለባት በቀኝም በግራም የዘይት

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ቋላላት ወአቤሉ በእንተ ምንት ከመዝ ይትኬነኑ ወያቤለኒ.
በእንተዘአበሰ በቤተመቅደስ ዘኢይደሉ በከህነት ወበእንተ ዘነሥኡ
ሀልያን በከህነት ወአለመኑ ዘይበውው ውስተ ቤተመቅደስ ወይቤለኒ
እለወለዱ በአስኬማሆሙ ወውእቱሂ ወልደ ጎድገት ወአፈ ላዕላሰ
ወቤሐመ ወጾመመ እዝን ወጸምላጠ ሳይን ወስቡረ እግር ወወልድ
ቁጻር አው ባዕላየ አው ነዳየ አለ ያበውው በሀልያን።

፫. ከዘስተጋላውም ብዙ ሰው ያስበት የእላት ወንዝ አየሁ እነዚህንም
በእላት አትሮንስ አስቀምጠዋቸዋል የሚመራኝ ባልደረባዬ መልአኩን
ጠየቅሁት እንዲህ አልኩት እኚህ እነማን ናቸው ፍጻቸውስ ይህን
ያህል የሆነ እነማን ናቸው አልኩት ቋላላት ናቸው አለኝ ይህን ያህል
የሚቀጡ ስለምን ነው አልሁት ስለበደሉ አለኝ ይኸውም በቤተመቅደስ
በክህነታቸው የማይገባ ሥራ ስለሠሩ መማለጃ ስለተቀበሉ ነው አለኝ
ወደ ቤተመቅደስ የሚገቡ እነማን ናቸው አልሁት መለሰልኝ እንዲህ
አለኝ በምንኩስናቸው የወሰዱ ናቸው ይኸውም ወልዶ መጣል ነው
አፈድጓ፣አፈለምባድ፣ ደንቆሮ፣ ድዳ ፣ዓይነ መጭማጫ፣ እግረ ሰባራ፣
ያልተጠመቀ ልጅ ባለፀጋም ቢሆን ድሀም ቢሆን ይህን ሁሉ መማለጃ
የተቀበሉ ቤተመቅደስ የሚያስገቡ ናቸው አለኝ።

፬. ወድጎረው አርአየኒ ባሕረ እላት ዓቢይ ወይነብሩ ብዙኃን በመንበረ እላት
ወይውኃጦሙ ፈለገ እላት ወአቤሉ አለመኑ ይትኬነኑ በዝንቱ ዓቢይ ኩነኔ
ወይቤለኒ መምህራን ወሊቃውንት ወአቤሉ በእንተ ምንት ይትኬነኑ።

፭. ከዚህ ቀጥሎ የእላት ባሕር አሳየኝ በእላት ዙፋን የተቀመጡ ብዙ ሰዎች
አልብት እነዚህም የእላት ወንዝ የዋጣቸው ናቸው በዚህ ጽኑ ፍጻ የሚቀጡ
እነማን ናቸው ብዬ ጠየቅሁት መምህራንና ሊቃውንት ናቸው አለኝ ስለምን
ይቀጣሉ አልሁት የሚፈረድባቸውስ ለምን ነው አልሁት።

፮. ወይቤለኒ አጸርጌ ባሕቲቶሙ ይበልው ወአሥራተ ቤተክርስቲያን
ባሕቲቶሙ ይበልው ወዘሞተ ነዳይ በሀገሮሙ ኢያቀብሩ ወበሕገ ቀኖና
ኢያምሕሩ ፍናተ ሕይወት ለአስዛብ ወአለኢመሐሩ አክብሮ ሰንበታት
ወኢያዜሉ ወመምህራንሂ ዘአመንኩሉ ወዘኢገሠገሠ ያቂቆሙ አመሂ
ዕደው ወአመሂ እንበት።

፯. ተረቆን ብቻቸውን ይበላሉ የቤተክርስቲያንን አሥራት ብቻቸውን
ይበላሉ በአገራቸው ድሀም ቢሞት አይቀብሩም በመጽሐፉ ቃል
ድኅነት የሚገኝበት ወንጌልን ለአሕዛብ አያስተምሩም ሰንበታትንም
አክብሩ ብለው አያስተምሩም አለኝ ልጆቻቸውን ሳይሠሩ (ሳይቀጡ)
ሳይፈቅዱ ያመነኩሱ ወንድም ሴትም ቢሆኑ መምህራን ነን አያሉ።

፰. ወአምድጎራሁ አርአየኒ አሳተ ወጸድፍ ዓቢይ መምሉዕ ሰብእ
ውስቴቱ እንዘይኩስትሩ አፍሐመ እሳት በእደዊሆሙ ወይቀድሁ
በአጻብኢሆሙ አሰራብ አሳት ወያውህጦሙ ፈለገ እሳት ኩለንታሆሙ
ወኢይትአወቅ አፋሆሙ ወአቤሉ አለመኑ ይትኬነኑ ውስተዝንቱ ኩነኔ
ወይቤለኒ አለያጣበሉ ድንግልናሆሙ በዕበደ ዘአንዘለለ ያስተዋስብዎሙ
አበዊሆሙ።

፱. ከዚህ ቀጥሎ ታላቅ የእላት ጉድጓድ አሳየኝ በውስጡም በአጃቸው
የእላት ፍህም የሚጠርጉ እላት በአጃቸው የእላት ጉርፍ የሚጠርጉ
ሰዎች በውስጡም ሞልተዋል ሙላ ሰውነታቸውን የእላት ባሕር
የዋጣቸው ናቸው ቋንቋቸውም አይታወቅም የሚቀጡ እሊህ እነማን
ናቸው አልሁት እናትና አባቶቻቸው ሳይድሯቸው በምድረበዳ
ድንግልናቸውን ያስወሰዱ ናቸው አለኝ።

፲. ወዓዲርአኒ ዐሥሩ ዓቢይ ወዓቢይ ግበ እሳት ውበዙኃን ሰብእ
(አህዛብ) ውስቴቱ በአልበሶሙ ጉልቁ ውስቴቱ፡ ቦ ዘይውህጦሙ እስከ
ክሳውዲሆሙ ወቦ ዘይውህጦሙ ኩለንታሆሙ ወአቤሉ ዘመጠንዝ
ዓቢየ ኩነኔ ይትኬነኑ በእንተ ምንት።

፲፩. ጳግሙኖ ላዩ ገደል ታቹ የእላት ጉድጓድ አየሁ በውስጡ ስፍር ቁጥር
የሌላቸው ብዙ ሰዎች አለብት እስከ እንገታቸው የዋጣቸው አሱ መላ
አካላቸውንም የዋጣቸው አሱ ይህን ያህል ጽኑ ፍርድ የሚፈረድባቸው በምን
ነገር ነው አልሁት።

፲፪ አሙሥአኒ ወይቤለኒ ዘያወህጦሙ እስከ ብረኪሆሙ ዘይትናገሩ ነገረ ፅሩዓ
በቤተክርስቲያን ወዘይውህጦሙ እስከሐቁሆሙ አለይዜምው በቤተክርስቲያን
ምስለአንስት ወዘያውህጦሙ እስከ እንግድኒቲሆሙ አለየሐምዩ ቢጸሙ
በቤተክርስቲያን ወአለሰ ይውህጦሙ እስከ አፋሆሙ እስከ ክሣውዲሆሙ
እምድኅረ ነሥኡ ቁርባነ እለይትናገሩእንዘለ ይቀደሙ ሕብእተ
አውዘይትወሐጥ ወእምእለ

ያቋርሩ ማየ ወእሉ ይትዋሐጡ ኩሉንታሆሙ ወይቤለኒ እለይዜምው ምስለተባእት ከመእንስት።

፰. መለስልኝ እንዲህ አለኝ እስከ ጉልበታቸው የዋጣቸው በቤተ ክርስቲያን ሞዛ ፈሞ የሚናገሩ ናቸው እስከ ወገባቸው የዋጣቸው ከሴት ጋር በቤተ ክርስቲያን የሚሰለኑ ናቸው እስከ ደረታቸው የዋጣቸው በቤተ ክርስቲያን ባልጀራቸውን የሚያሙ ናቸው እስከ አንገታቸው እስከ አፋቸው የዋጣቸው ግን ሥጋ ወደሙን ተቀብለው ማየ መቁረር ላይጐነጩ እህል ላይቀምሱ የሚናገሩ ናቸው አለኝ ሁለንተናቸውን የተዋጡትስ እንግን ናቸው አልሁት እንደ ሴት ወንዱ ከወንድ የሚደርሱ (ግብረሰዶም የፈጸሙ) ናቸው አለኝ።

፱. ወድጎሬሁ ርኢኩ ጸድፈ ዓቢየ ወግበእሳት ይትከረይ ውስቴቱ፲፱ሺ፰ሺ ዓመት ዘኢይትከሃል በጺሖቱ እማዕምቅቲሁ ወእቤሎ አለመኑ ይበውዑ ወይነብሩ ውስተዝ ፈለግ ወይቤለኒ አለይዜምው ምስለ ሐራስ ወትከተ ደም ወምስለ ጽዕልት ወአለያወስቡ በድነ ብእሲት ወአለያወስቡ ብእሲተ አባሆሙ ወእጉሆሙ ወእለይዜምዉ ምስለ ወሰቶሙ ወምስለ ወሰተ አጉሆሙ ወእለ ይዜምዉ ምስለ እንሰሳ ወአራዊት ወዝንቱ ኩነኔሆሙ ለእሉ።

፲. ከዚህ ቀጥሎ ላዩ ገደል ታቹ የእሳት ጉድጓድ ከጥልቀቱ የተነሣ ፲፪ሺ፰ሺ፭ ዓመት ቢቆፍሩ የማይደረስበት ጉድጓድ አየሁ ከዚህ ውስጥ ገብተው የሚናሩ እንግን ናቸው አልኩት መለሰልኝ እንዲህ አለኝ ከእርሷ (ከግዳጅዋ) ካልነፃች ከአውታታ፣ ከገለሞታ ሴት ጋር የሚሰለኑ ናቸው አለኝ በሞተች ሴት የሚደርሱ ከእንጀራ እናታቸው (ከአባታቸው) ሚስት የሚደርሱ ከወንድሞቻቸው ሚስት የሚደርሱ ከሴት ልጃቸው የሚደርሱ፣ ከወንድሞቻቸው ልጆች የሚደርሱ፣ ከእንስሳ ከአራዊት የሚደርሱ የእነዚህ ቅጣታቸው ይህ ነው አለኝ።

፲፩. ወእምዝ ርኢኩ ፀድፈ ዓቢየ ወጽልሙተ እሳት ወበህየ ርኢኩ ብዙኅ ሰብእ ውስቴቱ ወእቤሎ አለመኑ ይበውዑ ውስተዝ ፈለግ ወይቤለኒ አለያመልኩ በአዕባን ወበእንሰሳ በዝንቱ ይትኬነኑ።

፲፪. ከዚህ ቀጥሎ ዉኃለግና እሳት ያለው ታላቅ ገደል አየሁ

በውስጡም ብዙ ሰው አለበት ወደዚህ ገደል ገብተው የሚናሩ እነማን ናቸው አልሁት በደንጊያ፣ በእንሰሳ፣ የሚያመልኩ በዚህ ይቀጣሉ አለኝ።

፲፫. ወእምዝ ርኢኩ ዕፀ ዓቢየ ዘኩሉንታሁ እሳት ውስቁላን ውስቴቱ ብዙኃን ሰብእ ህየ ወአክይስተ እሳት ይበልእሙ ወእቤሎ አለመኑ እሉ ኢኮይትኬነኑ በዝ ፀጥግ ኩነኔ ወይቤለኒ መበለታት ወመነኮሳት አለያደ ነው ወይፀንሱ ወያሰተዩ ፈውሰ ወይቀትሉ ደቂቆን።

፲፬. ከዚህ በኋላ ሁለንተናው እሳት የሆነ ታላቅ ዕፅ አየሁ በዚያም ላይ ብዙ ሰዎች ተሰቅለውበታል የእሳት እባቦች ይበሉአቸዋል በዚህ ጽኑ ፍርድ የሚቀጡ እነዚህ እነማን ናቸው አልሁት ከፀነሱ በኋላ መድኃኒት እየጠጡ የሚያስወርዱ ልጆቻቸውን የሚገድሉ መበለታት፣ ጋለሞቶች መነኮሳት ናቸው አለኝ።

፲፭. ወእምዝ ፀርኡ እሙንቱ ጎበ እግዚአብሔር እመሂ ንኩን ሠናያን ወእመሂ እኩያን ኢኃደጉነ ንልሐቅ ክፍለነ በልዑ አራዊት ወክፍለነ በልዑ ከለባት ወዘይጤሀብሥሙሰ ለእሙንቱ ሕግናት ለጥልምያክለ ወለበዊሆሙሰ በዝይትኬነኑ።

፲፮. ከዚህ በኋላ እነዚያ እያስወረዱ የጣሏቸው ሕፃናት ወደ እግዚአብሔር ጮሁ በጎሥችም ብንሆን ክፋዎችም ብንሆን እናድግ ዘንድ አልተውንም እኩሌታችንን ውሾች በሉን ተቦጫጨቁን ኩሌታችንን አራዊት ማለት ጅቦች በሉን እነዚህን ሕፃናት ለጥልሚያክለ የሚሰጡአቸው አባቶቻቸው ግን በዚህ ይቀጣሉ።

፲፯. ወካዕበ ርኢኩ ፀድፈ ዓቢየ ወአብህርተ እሳት ፴ ወብዙኃን ነገሥት መመኪንት ወዓበይት ውስቴቱ ወእቤሎ አለመኑ ይትኬነኑ በዝኩነኔ ወይቤለኒ ነገሥት ወመኪንት ወመሳፍንት ወዓበይት አለይበልዑ ማዕኵተ ወያማስኑ አብያተክርስቲያናት ወይበረብሩ አብያተ መበለታት ወያጠፍዑ ዓለመ ወኢያፈቅሩ ዕንለማውታ ወኢይሁቡ ምፅዋተ እንዘ ቦሙ እምዝወሀቦሙ እግዚአብሔር ወዝኩሉ ኩነኔሆሙ ለነገሥት ወመኪንት ወመሳፍንት

፲፰. ከዚህ ቀጥሎ ታላቅ የእሳት ባሕር አየሁ በውስጡም ታላላቅ ነገሥታት መኪንት መሳፍንት አሉ ተፈርዶባቸው፡ በዚህ የሚቀጡ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

እንግን ናቸው አልሁት መግለጻ የሚቀበሉ ቤተክርስቲያንን የሚያጠፋ የድሆችን ቤት የሚቦረብሩ ሰውን የሚያጠፉ ድኃአደጉን የማይወዱ ገንዘብ እያሳቸው የማይመጻውቱ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ሁሉ የማይሰጡ የነገሥታት የመኳንንት የመሳፍንት ቅጣታቸው ይህ ነው አለኝ ።

፲፬. አሌ ለክሙ አለታማስኑ ዓለመ አሌ ለክሙ አለታማስኑ በመላላ ልህኩተ እግዚአብሔር አሌ ለክሙ ነገሥት ወመኳንንት ወመሳፍንት እለተሐንፁ አብያተ ወእንተ ውስጥክሙ አታፈቅሩ ካህናተ ወዲያቆናተ ትመስሉ ከመንዝብ ዘአልበ መሳር ወትመስሉ ከመቀሉት ዘአልበ ማይ።

፲፭. ዓለምን የምታጠፉ እግዚአብሔር የፈጠረው አካላችሁን በምላጭ የምታጠፉ የሰው ገንዘብ የተቀበላችሁ ቤት የምትሠሩ ነገሥታት መኳንንት መሳፍንት ወዮውላችሁ ውስጣችሁን ቢመረምሯችሁ ግን ግር የሌለበት ንብ ያለበት ቀፎ ትመስላላችሁ ካህናትን ዲያቆናትን የማትወዱ ባዶቀፎን ትመስላላችሁ ዳግመኛ ውኃ የሌለበት እንስራን ትመስላላችሁ።

፲፮. አሌለክሙ ነገሥት ወመኳንንት ወመሳፍንት አለኢታድጎኑ ግቱዓነ ወምስኪናን ወዘኢትምሕሩ ነዳየ ወጽኑሰ።

፲፯. የተገፋውን ጦም አዳረውን የማታድኑ ለተቸገረው የማትራሩ ነገሥታት መኳንንት መሳፍንት ወዮላችሁ።

፲፰. አብዳን ይመስለክሙኑ ዘታመስጡ በብዕለ ታዕካ መንግሥተ-ክሙ ይመስለክሙኑ ዘትሰውዑ ውስተ መንግሥተሰማያት ወኢይወርድ ምስሌክሙ ኩሉ ክብረ ቤትክሙ መንግሥትሰ ዘበምድር ይትረሣእ እስመ ኃላፊ ውእቱ ንብረተ ዝንቱ ዓለም ዓለሙኒ ኃላፊ መንግሥቱኒ ኃላፊ እስመኩሉ ከመልብሰ ይበሊ ወከመ ሞጣህት ይትዊለጥ/ጡ/ ወይዌልጦሙ ትጠውሞሙ ወይጠወሙ።

፲፱. እናንተ ሰነፎች በመንግሥታችሁ ገናንነት ከቅጣት የምታመልጡ ይመስላችኋል ወይስ በጌትነታችሁ መንግሥተ ሰማያት የምትገቡ ይመስላችኋል በዚህ ዓለም ያለ ባለፀግነታችሁ አብሯችሁ ወደ መቃብር አይወርድም በዚህ ዓለም ተዘንግቶ ይቀራል እንጂ የዚህ ዓለም ንብረት

ሁሉ ኃላፊ ነውና ዓለሙም ያልፋል መንግሥቱም ያልፋል ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃልና ሁሉም እንደ መጋረጃ ይጠቀለላል/ሱ/ እንደ ሸማሌ መጋረጃ ተጠቀልላችዋለህ ይጠቀለላሉ/ሱ/ እንደ ሁሉቱን ከአራት አራቱን ከስምንት ጠቅልለው በሳጥን እንዲያኖሩት አንተም ሰዓቱን በዕለት ዕለቱን በወር ወሩን በዓመት ዓመቱን በሺሺ ፯ቱን ሺ በስምንት ሺ ጠቅልለህ በሕልፈት ሣጥን "ሣጥን" ትወስነዋለህ።

ምዕራፍ ፩

፩. ብፁዓን እለእስማዕዎ ለእግዚአብሔር በሕይወቶሙ ብፁዓን ነገሥት ለኢያጽንኑ ፍትሐ ብፁዓንሰ ነገሥት እለ ያፈቅሩ ነዳያነ ወምስኪናን ብፁዓንሰ ነገሥት እመረሰይዎ ለጥበብ ከመመዝገብ ምሉዕ ብፁዓንሰ ነገሥት ለአእምሮ ሀገሪቶሙ ረሰይዎ ብፁዐንሰ ነገሥት እለ ወሀቡ ኩሉ ንዋየ-ሙ ቤዛ ነፍሶ-ሙ እእሚሮ-ሙ ከመኩሉ ዓለም ኃላፊ ወርቅሰ ከንቱ ወአልባስኒ ይበሊ።

፪. በሕይወተ ሥጋ ሳሉ በሥራቸው ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው፡ ፍርድ የማያጓሉ ድኃውን ጦም አዳሪውን የሚወዱ የሚረዱ ነገሥታት ንዑዳን ክቡራን ናቸው እውቀትን እንደማያልቅ ድልብ የሚያደርጓት ነገሥታት ንዑዳን ክቡራን ናቸው ሀገራቸውን በእውቀት ገንዘብ የሚያርጓት ዓለሙ ኃላፊ ጠፊ መሆኑን አውቀው ለነፍሳቸው ቤዛ ሊሆን ገንዘባቸውን ለነዳያን የሚሰጡ ነገሥት ንዑዳን ክቡራን ናቸው ወርቁ ከንቱ ነው ይጠፋል ልብሱም ያረጃል ያልቃል ብለው።

፫. አሌ ለክሙ ነገሥት እለትትሐየዩ ላዕለ ልሕኩተ ፍጥረተ እግዚአብሔር እንትሙ ለምንት ትትዔበዩ ላዕለ ርእየት።

፬. በእግዚያብሔር ፍጥረት ላይ የምትታበዩ ነገሥታት ወዮላችሁ፡ በእግዚያብሔር ፍጥረት ላይ ለምን ትታበያላችሁ።

፭. አሌ ለክሙ ነገሥት ወመኳንንት እለ ታማስኑ ፍጥረተ እግዚአብሔር በመላላ ወዘንስይፍት ወኢትክሱ አሐተ ሥእርተ ርእሱ ለብእሲ ኢፀዓዳ ወኢጸሊመ ረሰዮ ኢሰማዕክሙኒ ዘይቤ መጽሐፍ እም ፯ወ፱ነገደ መላእክት ፩ይክብር።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

፫. የእግዚአብሔርን ፍጥረት እኩል በመላዋ ገጸ-ምድር የምትኖሩ ሚሊዮን ሰዎች ሁሉ ለሁሉ የምታስቡ ነገሥታትና መሪዎች መሳፍንት ክፉው ክፉት ፀጉር እንዲቸን ሰንሂ ነጭ ወይም ጥቁር ማድረግ እደሚችሁም ከገዛች ነገደ መላእክት እንዳከበር አታውቁምን ማለት ክፉ ክማይሹ ከገዛች ነገደ መላእክት ይልቅ ክፉ ገፀተ የተገኘ አሞ እንዲከሆኑ አታውቁምን።

፬ አል ለክሙ ነገሥት አለ ይሔርፁ እምታሕቴክሙ በእ ከሥልክሙ ወታግስት ዓለመ ለእመ አክሥለክምሙ ኖሎሙ ይትነገሥ እግዚአብሔር ዓለሊክሙ።

፮. ክሊትችሁ ያሉ ሹምቻችሁ የሰውን ገንዘብ ሲዘርቱ ሲበረብሩ ያልሠራችኋቸው ያልቀባችኋቸው ነገሥታት መሳላችሁ እንዲህ እያደረጋችሁ ዓለምን ታስከፋላችሁ እናንተ ከሥልጣኒችሁ ቢኮን ያለ ሹምቻችሁን የሰው ገንዘብ ሲዘርቱ ሲበረብሩ ሳትመረ ተው ሳትቀሚቸው ቁትቀሩ እግዚአብሔር ፍሩውን ከናንተ ያመረመረል ማለት በእነሱ ምክንያት እናንተን ተመራምሮ ያጠፋችኋል..

፭. ወእነ ዛርክ ርኢኩ ከንኔያቲሁ ዓቢያተ ወገሩመ ዘዘዘ እሀ መሳፍርነ ግርግሁ ወርእኩ አደባረ ዓቢያንወምስዕ ውስቲቶሙ እሳት ነክ ያ ወሰመሳፍንት እንዘ ይደፍናሙ ጽሕረተ እሳት ወእዘሉ ለመሳእክ እለይመርሐኒ ምንትኑ እሉ ሰብእ እለ ሀለው ውስተ ዝንተ ከንኔ መፍርሕ ወመደንግጽ ወይብለኒ ነገሥት ጠዋያን አለያግስን ነሰመ ወይብረብሩ አብያተ ክርስቲያናት።

፩. እኔ ዛርክ አየራስ አየራሳቸው ልዩ የሚሆኑ ከግርማነ ው የነገሥ የሚያስፈሩ ቅጣቶችን አየሁ ጻገሙኖ ዘውሶባነው አሳት የተመላባቸው ታላላቅ ተራሮች አየሁ በጋን ውስጥ ያለ አሳት የሸፈናቸው መሳፍንትን አየሁ የሚመራኝ ባልደረባዬ መልአኩን እንዲህ አልሁት በዚህ በሚያስፈራና በሚያስደንግጥ ቅጣት ውስጥ ያሉ እሊህ ምንድናቸው አልሁት፡ ዓለምን የሚያጠፉ አብያተክርስቲያናትን የሚበረብሩ ጠማሞች ነገሥታት ናቸው አለኝ።

፯ ወድኅሬሁ ርኢኩ ግዐ እሳት ዓቢይ ወግሩም አደባረ እሳት መምስዕ ውስቱቱ መነኮሳት ዕድ ወእንስት ወእከይስተ እሳት ጥብሰል በአልባ ዚሆሙ ወአፍያተ እሳት ይነድፍሙ ወእከልብተ እሳት

ይበልዕሙ ወዘኮናሁ እሳት ይረግዘሙ ወመርግሐ አሳተ ይወድቁ ዓቢሙ ውዕ ነዘ እሳተ ግዐ ይውኅሥሙ ወእዚሉ ለውእቱ መልአክ ዘይመርሐኒ አለመነ ይንገረነኒ በዘጸሞግ ከንኔ።

፱. ዘዚህ በእላ ታሳቶ የእሳት ጉድጓድ የእሳት ተራራ አየሁ በውስጡ ወንዶችም ሴቶችም መነኮሳት ሞልተውበታል የእሳት እባቦች በልበሳቸው ላይ ተጠምጥሞባቸዋል የእሳት ጊንጦች የእፉኝት እባቦች ያነድፋቸዋል የእሳት ውሾች ይበሏቸዋል በእሳት ጦር ይወጋቸዋል የእሳት መረግ ሰናፍ በላያ ይወድቅባቸዋል የእሳት ውኃ የእሳት ጉድጓድ ያውጣቸዋል የሚመራኝ ባልደረባዬ መልአኩን በዚህ ፅኑ ፍርድ የሚቀጡ አንግን ናቸው ብዬ ጠየቅሁት።

፲. ወየብለኒ መነኮሳት እሰያብሉ መነኑ ዘንተ ዓለመ ወእመነኑ ወእያንጸሉ ምክንያትሙ ወተመለሱ ከመ ስብእ ዓለም ወእውሰቡ እንስተ ወሠለፍ ወረሥሉም ለእግዚአብሔር በመዋዕለ ሕይወቶሙ ወተመለሰ ከመ ከልብ በደበለ ዲበ ቀያሁ ወተመለሱ ከመ እንስሂያቲት ሐረውሮ ወቦሊሳ ንብእት ዲበጽላሕ ደብር ወተመለሱ ከመ ብእስ ተ ለሥ ዝኮን ሐውልተ ዓው ወነዕበ ተመለሱ ከመእዚአስ-ም ወተሃሥ እም ተእዝዘ አዙሁ ወከመዝ ርኢኩ ከንኔሆሙ ለእለ

፲፩. ይህን ዓለም መነን ብለው ያልመነኑ ናቸው ምንኩስናቸውን ከኑሮያት ያላነጻ ውነለም ሰው ተመለሱ ማለት ከመነኮሱ በኋላ ሚስት አግብተው ልጆ ወለዱ በሕይወት በሚኖሩበት ዘመን እግዚአብሔርን በነገት ችል አሉት የተፋውን መልሶ እንደሚበላ ውሻ ሆኑ ከተመለሰ በኋላ በሥራ እደምትለወስ እሪያ ሆኑ ሐውልተዒው (የፈጠው ድንጋይ) (ሐውልት) እንደሆነች እንደ ሉጥሚስት ሆኑ ማለት እሳ መላእክት ሦረሽ አትይ ቢሏት ሀገሯን ዙራ አይታ ሐወልተዒው (የፈጠው ሐውልት) ሆና እንደቀረች እናንተም ከመነናቹ በኋላ ወደ ዓለም ብትመለሱ ከንቱ ትሆናላችሁ ብሎ ጌታ በወንጌል የመናንያን ምሳሌ አድርጓታል በዚህም ላይ ከአባቱ ትእዛዝ እንደወጣ እንደ አቤሴሎም ናቸው ማለት ከእግዚአብሔር ትእዛዝ የወጡ ናቸው የነዚህ ፍርዳቸው ይህ ነው አለኝ፡

Scanned by DocumentScanner | Lufick

፰. ወካሰበ ርኢኩ ሰብአ እንዘ ይረይጽምሙ በአህጎ እሳት ወእቤሉ አለመኑ ዘመጠነሽ ኩነኔሆሙ ወይቤለኒ ጲያቆናት አለ አያበውኡ መሥዋዕተ ፍቡነ ውስተ ቤተመቅደስ።

፰. ዳግመኛ በእሳት ጦር የሚወጓቸው ሰዎችን አየሁ ይህን ያህል ፍርድ የተፈረደባቸው እነማን ናቸው ብዬ ጠየቅሁት ወደ ቤተመቅደስ ገብተው መሥዋዕቱን ለማዘጋጀት የማይፈጥኑ ጲያቆናት ናቸው አለኝ።

፱. ወካሰበ ርኢኩ እንዘ ይሰቅልዎሙ በሐብለ እሳት በእገረሆሙ ላዕለ ርእሶሙ ቀልቁሊተ ወእቤሉ አለመኑ ይትኬነኑ በዘመጠነገ ኩነኔ ወይቤለኒ ካህናት አለ ኢያቁርቡ ቁርባነ በጊዜ ይሠርቅ ፀሐይ በቀዳሚት ሰንበት ጊዜ ፲ቱ ሰዓት ወዝ ኩነኔሆሙ።

፲. ዳግመኛ በእሳት ገመድ አስረው ሰቅለው በእግራቸው እራሳቸውን ቁልቁል የሚረግጧቸው ሰዎችን አየሁ እንዲህ ባለ ፍርድ የሚቀጡ እነማን ናቸው ብዬ ጠየቅሁት እነዚህ በአለተ ቀዳሚት በ፲ ሰዓት አሁድ በነግህ መስዋዕት የማያቀርቡ ካህናት ናቸው የነዚህ ቅጣታቸው ይህ ነው።

፲፩. ወርኢኩ ሰብአ እንዘ ያለክፍሙ እሳት ወያበልዕሙ ወያለትይሙ ጽዋዓ እሳት ወእቤሉ አለመኑ ይትኬነኑ በዘመጠነገ ኩነኔ ወይቤለኒ አለሂ ካህናት ወዲያቆናት አለተዓደዉ ለግብረ መልእክት አለአሠራን አሙንቱ ወዝንቱ ኩነኔሆሙ።

፲፪. ከዚህ ቀጥሎ የእሳት ምግብ የሚያበሏቸው የእሳት መጠጥ የሚያጠጧቸው ሰዎችን አየሁ በእንዲህ ያለ ፍርድ የሚቀጡ እነማን ናቸው አልሁት የተቀጠሩበትን የቤተ እግዚአብሔርን አገልግሎት ያፈረሱ ቸል ያሉ ካህናትና ዲያቆናት ናቸው አለኝ ቅጣታቸውም ይህ ነው አለኝ፡

፲፫. ወካሰበ ርኢኩ እንዘይመትርዎሙ እደዊሆሙ ወእቤሉ አለመኑ ምቱራን እድ ወይቤለኒ አለይጽሕፉ ክርታሰ ወይቀርጹ አምክርታስ ወካሰበርኢኩ እንዘይወጽ አምአፉሆሙ እሳት ወእቤሉ አለመኑ ይትኬነኑ ጠቃብያን አለይጠቅቡ አልባሰ ወአለያተርፉ አፍትልተ።

፲፬. ዳግመኛ እጃቸውን እየቆረጡ የሚጥሏቸውን ሰዎች አየሁ አሏህ እጃቸውን የተቆረጡ እነማን ናቸው አልሁት ያልተጻፈበት ወረቀት እየቀረጹ እየጻፉ የሚሰጡናቸው አለኝ ከዚህ ቀጥሎ ከአፋቸው እሳት የሚወጣ ሰዎችን አየሁ በእንዲህ ያለ ፍርድ የሚቀጡ እነማን ናቸው አልሁት ልብስ እየሰፉ የተረፈውን ፈትል ከልብሱ የተረፈውን ቁርጥራጭ የሚያስቀሩ ናቸው አለኝ።

፲፭. ወዓዲ ርኢኩ ዓምደ እሳት ስንሰላን ውላህበ እሳት የሀውከሙ ወኩሉ ፍጥረት ውግደጽሩ የሐውር ቅድሜሆሙ ወሶበ ፈቀዱ ይብልዑ ወይሰተዩ ይጥሄይ እምኔሆሙ ወእቤሉ አለመኑ ይትኬነኑ አለይሥእሩ ጾመ ረዙስ ወባንርብ ወአይትዓኪዙ አስከ ፱ ሰዓት ወበ ዓቢይ ጾም አስከ ዕርበተ ፀሐይ ወዘንተ ኩሎ አርአየኒ ሱቱኤል መልአክ።

፲፮. ዳግመኛ የእሳት ምሰሶ አየሁ ከእሳቱ ምሰሶ ላይ እርስ በርሳቸው የተያያዙ ላህበ እሳት የሚያውካቸው አሉ ፍጥረት ሁሉ ጽሩይ ውኃም በፊታቸው ይሄዳል ሊበሉ ሊጠጡ በወደዱ ጊዜ ከነሱ ይሸሻል ማለት አይሰጣቸውም በዚህ ፍርድ የሚቀጡ እነማን ናቸው አልሁት አስከ ፱ ሰዓት ታግሦ መቀየት ተስኗቸው የዓርብና የረቡዕን ጾም የሚሽሩ ናቸው አለኝ በዓቢይ ጾምም ፀሐይ እስቲገባ መጾም ተስኗቸው ዓቢይ ጾምን የሚሽሩ ናቸው፡ ይህን ሁሉ ሱቱኤል የሚባል መልአክ አሳየኝ።

ምዕራፍ ፭

፩. ወዓዲ ርኢኩ ዓቢይ ኩነኔ ጎድም በ፯ማኅተም ወይቤለኒ ትጠብዕኑ ባሮክ ከመ አርኢክ ዘንተ ኩነኔ ዓቢየ መፍርሐ ወመደንግፀ ወእቤሉ በልኢ እግዚአየ አርአየኒ።

፪. ዳግመኛ በጌቱ ማኅተም የታተመ ማለት በፍጹም /በፅኑ/ ቁልፍ የተቆለፈ ቤተገሃነምን አየሁ። ባሮክ ይህን የሚያስፈራ የሚያስደነግጥ ጽኑ ፍዳ አሳይህ ዘንድ ትራቀቃለህ ትጠብቃለህ ትጨከናለህ አለኝ ጌታዬ በል አሳየኝ አልሁት።

፫. ወይቤሉ ለመልአክ ገሃነም አርኁ ማኅተመ ወይርአይ ባሮክ ፍቁረ እግዚአብሔር ወአርኃወ ማኅተመ ወወጽአ ኩነኔ አይጎ ዘይብልዎ ገሃነም ወዓቢይ ቁሩ አስሐትያሁ ለማይ ወምድር እምአመ ተፈጥረ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

እነኔ ኄኖቶዓሊም ሙሴ፡ቶ ፀአየ እያከለ አሙቶየ ውኔ የዚአር'ሙ ያ'ክ እዳ መጫኒየ መመኔስ ቅዱስ ሐመጻት ኩሉ አሮ'ሚሃ ለሊአል ውሶኒአለኔም ወአሉሉ ምንት ስሙ ለዘ ኩነኔ ወአለ መኑ ይንብሩ ውስተቱ ።

፪. መልአኩ ሱቁኤል የገሃነሙን ሹም ጥልሚ'ኮስን እንዲህ አለው የገሃነም ቁልፍ ፍተና የአግዚአብሔር ባለሚል ባርክ ይይ አለጪ፡ ቁልፉን ፈትለት ግለት የገሃነምን ዙር ከፈተለት ገሃነም የሚሉት ጽኑ ፍርድ ያለበት ውኃ ታየ ይኼውም ውኃ ቀዝቀባነቱ ጽኑ ነው፡ ይላል አኒሐትያ ወትኑ ቁር ግፃሩ ነው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከነልቀተ ዓለም የውግ ፎለፎ ሊሞቀው አይችልም በእብ ወወልድ በመንፈስ ቅዱስ ዘንድ አያስቡትም ግለት አይቃስዘም የሊአልን አሙራጃዋን ግለት አፍአውንም ውስጢንም አየሁ ጮብኝሁ ከሆኑ በኋላ ባልደረባዙ ሱቁኤልን የዚህ ደይን ስሙ ምንድነው በውስጡስ የሚኖሩ እ ነማን ናቸው ብዙ ጠየቅሁት።

፫. ወደፊለኒ ለዝስሙ ገሃነም ወተንዝላት እለ ኢየአምኑ በቮ አካላት አኮነ ወልድኒ አኮነ መንፈስ ቅዱስኒ አኮነ ዘንተ እለ ደብሉ ይነብሩ ውስቱቱ ወዘዕሉ ውስቱታ አልዐ ትንሣኤ ሙታን ወዘአንተዝ ዘዘመ ይዜ ጻዊት በእንተዝ አይትነሥኡ ረሲዓን እምፍደን ወኢኃጥኦአን ውስተ ምክረ ጻድቃን ወዘንተ ኩሉ አርአየኒ።

፬. ይህ ደይን ስሙ ገሃነምነው በውስጡም የሚኖሩ በአካል ፎት በመለኮት ፩ ብለው የማያምኑ ወልድንም ወልድ አያደለም መንፈስ ቅዱስንም መንፈስ ቅዱስ አይደለም ይህን የሚሉ በውስጡ ይኖራሉ በዚህም ደይን የሚኖሩ ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ናቸው አለኝ ስለዚህም ጻዊት እንዲህ አለ ሕገ እግዚአብሔርን የዘነጉ ረሲዓን አይሁድ ከቁርጥ/ጽ/ ፍርድ አይድኑም አለ ኃጥአንም ጻድቃን በመከሯቸው ምክር ጸንተው አያኖሩም ይህን ሁሉ አሳየኝ።

፭. ወዓዲ አርአየኒ ሠናያተ ዓመታተ ወብዙኃን ፍቅረ አህፅ ወሥርናይ ወመዓር ወዘሊብ ይወርድ ወመንፈስ ቅዱስ ከመጠ ክረምት ጾም ወጸሉት ያሠምሩ ብአሊ ምስለብአሊቱ አብ ምስለ ወልዶ እም ምስለ ወሰተ ወለታ ወመነኮስ ምስለ ረድኡ እጉ ምስለ እጉነ ወአርክ ምስለ አርኩ ዘይጥእም ይትናገሩ እሚሃ ይትወለድ ክርስቶስ በሳ ስክዘ በአጽርቅት ተጠብለለ በበሕቅ ልሕቀ በሻከረምት በየርዳናስ

ተጠመቀ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት ወአገተኦደሮ ለዓ.ያበሉስ ወንብረ ሻዕለተ ወአምዴንፈዝ ዓርገ ውስተ ለማየት ወተኩነ ሉቱ መላእክት ወሰ.ቆን መላእክት ወኩሉ ፍጥረት በየዘወፎቱ ዓመት በአትማር አምዕርገቱ ለእግዚእነ አየሱስ ክርስቶስ የየሮ ዓመት በአትማር ጀመሮ ዓመት ዕሌኒ ንግሥት ኃሠሠት መስቀሉ።

፮. ኣግመሮ ያማሩ የተወደዱ ዘመናትን አሳየኝ ማለት ነገረኝ እህል ስንዴ መዛር ወቶት የሚበዛበት ዘመን ነው ብዛቱም በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ እንደሚወርድ እንደ ነበረምት ውኃ ነው ጾም ጸሎት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛሉ ወንድ ከሚስቱ ጋራ አባት ከልጁ ጋራ እናት ከልጅ ልጇ ጋራ መነኩሴ ከረዱ ጋራ ወንድም ከወንድሙ ጋራ ባልንጀራ ከባልንጀራው ጋራ የሚባባዩት ነገር ማለት ተስማምተው ደስ የሚያሰኝ ነገር በሚኒገሩበት ወራት ያን ጊዜ ጌታ ይወለዳል በጨርቅ ተጠቅልሎ በነል ተጥሎ ተገኝ ጥቶት ጥቂት እያለ አደገ በሟ ዘመን በዕደ ዮሐንስ በማሃ ሶርዳናስ ተጠመቀ በዘመነ ሉቃስ በወርኃ መጋቢት በሻኜቀን በመቮ ዓመት ከቮወር በአለተ ዓርብ ተሰቀለ ታሞ ሞተ ተቀበረ በሦስተኛው ቀን ተነሣ ተንሥኖ ዳያቢሉስን አሳፈረው ፵ ቀን በምድር ከቆየ በኋላ ወደ ሰማያ ዓረገ መላእክት ሊቃነ መላእክት ፍጥረት ሁሉ ተገዙለት ጌታ ባረገ ፻፵፯ ዓመት በአቅማር አቆጣጠር በ፻፫ዓ ዓመት አሁንም ዑንትማር አቆጣጠር በ፳፫ ዓመት ንግሥት አሌኒ መስቀሉን ፈለገች። ንግሥት አሌኒ መስቀሉን ያወጣችው በ፫፻፳፭ዓ.ም ነው ብሎ የተጠቀሰውን እትማር ይፈቷል።

፯. በውስቱ መዋዕል ነገሠ ቊጥብ አጠናበ ርቱዓ ሃይማኖት ወዘመዋዕሊሁ ኮነ ፍቅር ወሰላም ወተራከቡ አብያተ ክርስቲያናት ዘአመዝበሮሙ ጳዮቅልጥያኖስ ለልው ወዘዘኮ ፍቅር ወሰላም ወተኳሪኦሉት እስከ ንዛረ መስቀል ንጉሠ አክሱም በረ፻ መሠ ዓመት ተወሰከ ሉቱ አቅማር በእንተ ርትዕት ሃይማኖት ሠ ዓመት ፪ አስከ ይወርድ ሐመደ እምንዛረ መስቀል ፭፻፴፬ ዓመት ሐልቀ አቅማር ወዘዓመት ተሐጽጽ ፍቅር ወየሐልቁ ንውኖን ወየኃልፉ እምድር ወእልዐ ዘይተርፍ እምድር ወእምድረ ሐልቁ ጌራን ናሎት ወሊቁ ናሎት እለ ተንሥኡ ንውሳን ቂናጽል እለ ያማስኑ ዓለመ ወሰለዓመቁ የሐጽጽ ፍቅር ወታብታት እግዚአብሔር የዓርጉ ውስተ ሰማያት ወጸዮን ለማያዊት ዕክልሂ ወማደሂ በ፬ቱ ዕድ ይበዝኑ አብያተ ክርስቲያናት ይትሐነጻ ወበውስቴቶን ይትንበር ጸሎት ወቁርባን ወዕጣን ወመሥዋዕት።

Scanned by DocumentScanner | Lufick

፩. በዚያ ወራት ቀርነ ሃይማኖት የቆመለት ቈስጠንጢኖስ ነገሠ በሱም ዘመን ፍቅር እንድነት ሆነ ከሀጲ የሚሆን ጲዮትልጥያናስ ያፈረሳቸው አብያተ ክርስቲያናት ታነጹ የአክሱም ንጉሥ ገብረመስቀል አስቲነግሥ ድረስ ፍቅር እንድነት ተድላ ደስታ በገዙ ኖረ ፩፻፵ ዘመን ተጨመረለት ሃይማኖቱ ስለጸና ነው በመቶ ፵ ዓመት ሐመድ እስኪወርድ ድረስ ከገብረመስቀል ጀምሮ እስከ ፩፻፯ ዓመት ዓፄ ሥርዓ አለቀ ከዚያ ቀጥሎ ባመቱ ፍቅር ታኽለች ንሉላን ካህናትም ያልቀሰ አልፈው ሲሔዱ በቁጥር ያንሳሉ በምድር የሚተርፍ የለም ከዚህ በኋላ ደጋግ ነገሥታት የሠራዊት አለቆች ዓለምን የሚያጠፉ ጥቃትን ነገሥታት በተነሱ ጊዜ ማለት መናፍቃን ነገሥታት በተነሱ ጊዜ ሰለት ሰለት ፍቅር እያነሰ ይሄዳል የእግዚአብሔርን ማደርያ ታቦት ጽዮንን ያከብራሉ ሰማያዊት እላት ልአልት ናትና እህል ውሃ በፀትበፀ እጥፍ ደብዛሉ አብያተ ክርስቲያናት ይሠራሉ በውስጣቸውም ጸሉት ቁርባን ሰጣን መሥዋዕት ይደረጋል።

፪. ኢየንርግ ውስተ ስማይ እኩይ ምስለ ወሠናይ ወይክውኑ ካህናተ ወኢይትለአኩ ለቤተ ክርስቲያን ሐካይያን ወዘየጎብን ወዕቡያን ወጽሑግን።

፫. ክፉ ከበጉ ጋር ወደላይ አይወጣም ማለት ከክፉ ጋር የተሠዋ ማለት መሥዋዕት የማይሆነው አያርግም ክፋዎች ትቢተኞች ቸልተኞች ሰነፎች ካህናት ለክህነት አይበቁም።

፮. ወበውአቱ መዋዕል ይትፈጠሩ መምሕራን ሐሳሂያን ወኩሉ ያገብው ኀበ አስኪማ ለሊሆሙ ኢያድኅኑ ወለለ አተሙሂ ኢያድኅንዎሙ ወይሥእሩ ሰንበታተ ወበዓላተ ልደት ወጥምቀት ሽወፀ ዓመተ ምሕረት ይትፈሥሑ ዕወ ገዳም ወይትኀሠሩ ነሰ ፍጥረተ ሰብእ ወኩሉ ፍጥረተ እንስሳ ይገብው ውስተ ዘተዳግ ፍጥረቱ ወይነግሥ ብእሲ ጻድቅ ዘይቀንት ጽድቀ ውስተ ሐቂሁ ወይትዓወፍ ርትዓ ውስተ ገበሁ ወይሠርፅ ጽድቀ በመዋዕሊሁ ወያነግሥ ሣዓመተ ወብእትሜር ፩፻፵ ወ፫ ዓመት።

፯. በዚያ ወራት ሥራቸውን ቸል የሚሉ መምህራን ይነሣሉ ሁሉን ወደ ክፉ ስራቸው ወደእነሱ ይመልሳሉ እነርሱ ራሳቸውን አያድኑም የሚያስተምሯቸውንም አያድኗቸውም ይህም ይህ ነው ከዚህም ጋር

በዚህ ላይ እሱድ ቅዳሜን ይሽራሉ በዓላተ ልደት ወጥምቀትን ይሽራሉ ማለት አያከብሩም ሽ፬ት ዓመት ሲሆን የምድረበዳ እንጨቶች ደስ ይላቸዋል ፍጥረት ሁሉ ደስ ይላቸዋል የእንስሳ ወናኖች ሁሉ ወደቀደመ ተፈጥሯቸው ይመለሳሉ ማለት ፍጥረት ሁሉ እንደቀድሞ ደስ ይላቸዋል ደግ ንጉሥ ይነግሣል ጽድቅን ይታጠቃል ቅንነትን ይታናጸፋል ማለት እውነት ፍርደ ይፈረዳል ያን ጊዜ እነዚህ ሁሉ ደስ ይላቸዋል በሱ ዘመን ምግባር ትሩፋት ይሰራል ፸ዓመት ይነግሣል በአቅማር አቆጣጠር ፩፻፵፰ ዓመት ይሆናል።

፰. ወ ምድር [illegible] ዓመተ ይመጽእ ሐሰዊ መሢሕ እዝያህል ጊዜ መጽሐፍ ክርስቲያን ወሰንበር ብዙ ጉዞ ተአምራት መመንከራቱ ወ[illegible] ወሐሰ መንክሰ ምሥጢረ ወዘዘርኃ መንክሰ ኤላም ምኒሂ ዓመተ ብእኒ በሃም ወሰማኒ ዘሰ ነ ተ ዘ ሰ ሐጺሩ ዕደዊሁ ጸ ነጽሞን ወ[illegible] ዕገሪሁ ሥግሰሰ ሃ ነ ሰ ለ[illegible] ወይነግሥ ጊተ ዓመተ ወሰገሥ ንጉሥ [illegible] ወይነግሥ ወፈጸእንበሳ ጊተ ዓመተ ወዘ ሐ ሐ ወሰገሥ ጊዜ ካህናተ ወሚያቀርብ ጊ ነ [illegible] ወመንፈሳዊ ወመንፈሳውን ወዘዘርኃን ሠራዊተ [illegible] ወአስከሬማ ወዘርስትና ወያዘልሉ ለዘዘልዘ ንግሢ ዘንበ ክሡ በንጉሥ ወአዕረገ ውስተ ጻልሃ ወወሰሃ ብካሃ ወሥፃ መምነ ከሰሙ መንጉሥኒ ምስለሆሙ።

፱. እርሱ ፸ ዓመት ከገዛ በኋላ ክርስቶስ ነኝ የሚል ሐሳዊ መሲህ ይመጣል በምታት ብዙ ተአምራት ያደርጋል ወሐይን ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ጨረቃን ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ይመልሳል ማለት ወሐይንና ጨረቃን የፈጠርሁ እኔ ነኝ ይላል ቀኝ ዓይኑ በዲም የታሰለች ናት ቦ ፍጥሕት ይላል የፈለሰች ናት ቀኝ እግሩ ቀጭን ወላር ነው የእጁ ጥፍሮች እጆቹ ልምሾ የሆኑ የለለሱ ናቸው የእግሩ ጥፍር እግሩ እንደ ሚዛጅ ነው ማለት ጠማማ ነው ስልጣኑ ለሚላት የሚፋጠን ነው ሞቶ ሳለ ሕያው ነው ፮ ዓመት ይነግሣል ከዚህ በኋላ በፍጹም ቆጥሮ ፯ዓመት አለ እንጂ ፪ ዓመት ከመንፈቅ ነው በቅዱሳን ጸሎት /ጉወር ተኩል ይሆናል/ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ያስናብተዋል ማለት ያጠፋዋል ከዚህ በኋላ የአንበሳ ምሳሌ የሆነ በአንበሳ የተመሰለ ንጉሥ ይነግሣል ይኸውም በአቅማር አቆጣጠር ፰፻፯ዓመት ይሆናል የክሡት የዲያቆናት ጉባኤ ያደርጋል ማለት ካህናትን ዲያቆናትን

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ፍጥረትን እጂ እየቆጠሩት መኳንንትን ምኒሚን ጭፉ ሠራዊትን የሚመሩትን ሁሉ እነዚሚ ቀፎ የሚሞጉትን ክርስቲያኖችን ይጨካል ይሆን ሁሉ ይመራል ዓለምት በታ ሥልጣን ያለው እሱን እሚህ እሳው ይህ ሁሉ ተቀብል እሳው ተቀብሉም ወሲሩ ዓመጣጥው ጊዜ ያን ልጅነ እየቀት ሊለቅነው ሁቱ ንጉሥ እነርሱ ጋር ሞት ማለት አለ።

፪. ወደመጀመ ሚካኤል ምሳሌነት ሥነ [illegible] መደንገጫም ለአመንቱ ወደመነሮም ሁሉ [illegible]

፫. ክፎይ በጊዜ ሚካኤልና ንብርኤል ከሠራዊቶችቸው ጋር መጥተው እሚያን መከሩ የተቀበሉትን ሁሉ ተርፋ ይህ ወሳሳበት ወደኋት ይመለከቷል።

፫. ወሲምቱ ይኒምሪ አቆልቦን ጋኔን ሰምስኤሎ ኑሳልፍ ሰመጀመሪያ መደብሰው ቆሳትቱ ከመ ብርሃ ወሩውንጉ እነተ ወደሰማሪ ጀመ ትከተ መደንግም ጀዓመተ በኢየሩሳሌም ያፌ ንጉር መንበር ሊመ ነገሥ ሁሉና እንስት ሰፌፍ በማህ ወሰፌፍ በምሌት።

፮. ንዚህ ቀጥሎ ከርሱ ጋር አቆልቦን የሚባል ጋኔን ይዞ ይመጣል ሰባት ሰልፍ ከሮጌዓመት አለ ብዛታቸውን መናገር ነው ዋሻውን ጀደሱን እንደንሰባ እንደሽንዙቶ ይበሉታል አሳቱን ይውጣሉ የግዳጅ ጨርቅ ይሰሳሉ ደሙን ይጠጣሉ በንጉር የተመሰለ የሐሳዊ መሢህ ፊት አውራረ በኢየሩሳሌም ጀዓመት ይነግሣል በዚያ ተቀምጠ ከሴት የተመለደውን ሁሉ ያጠፋል በነግህ ዕልፍ በምሴት ዕልፍ ያጠፋል።

፲፩. ወአምድፊሁ ይነፍሕ ነፋስ ወያመዘብር አእጽምተ በብኔ አለ ውስተ መቃብር ወደነግሥ ጀዓመቱ ወአምድጎራሁ ይነፍሕ ሚካኤል ቀርን መጠነ ሰዓመት ወደሰፈያ ኩሉአ ጽምት ወደተጋብኡ ኩሉ ሥጋት ወዘገለሰ ጻፍሐተ ቀርን ሚካኤል መጠነ ሰ ዓመት ይትነሥአ ምውታን ከመቅጽበተ ዓይን ወቦ ፀሐይ እምፀሐይ ይጌይስ ከብሩ ወቦ ከክብ እምከክብ ይጌይስ ክብሩ ወይቀውም በኃጣር ወቦ በክብር ወይመጽእ ንጉሠ ሰማያት ወምድር ወይፈድዮ ለኩሉ በዘመ ምግባሩ ልቱ ስፍሐት ወአሥቱት።

፲፪. ከዚህ በኋላ ፅኑ ነፋስ ተነሥቶ በመቃብር ያሉ የሰውን አጥንት ሁሉ ይሰበስባል ፯ቀን ቆይቶ ሚካኤል ነጋሪቱን ይመታል ጌታ በዚህ ዓለም ሰ ዘመን በኖረው ልክ ነጋሪቱን ይመታል ማለት ንቃህ መዋቲ ይሳል በመጀመሪያውና በጀኛው አዋጅ አጥንት ሁሉ ሥጋም ሁሉ ይሰበሰባሉ በደኛው አዋጅ ሙታን ሁሉ የሰዓመት ጉልማሳ ያህል ሆነው ዓይን ከድኖ እስኪገልጽ ድረስ ማለት ፈጥነው ይነሣሉ መደመሪያ ጅግት ይታጣቸዋል በጀተኛ ሥጋ ተመርጕባቸው ቁርበት ይለብሳሉ ሥጋውም ቁርበቱም በተፈጥሮ የተሰጣቸው ገንዘባቸው ነው የተዘራው ፈርሶ በስብሶ የነበረው ሥጋ ታድሶ ይነሣል፡ ከዚህ በኋላ ጌታ ኢየሱን ፪ት ማዕዘን ካሳቸው አብያተነፍሳት ከፅቱ ማዕዘን ዓለም መጥተሽ እደረሰቸዉ እነርሱም አንቺን ተዋህደው ይነሡ ይላታል እርሷም መጥታ ታድርባቸዋለች እነርሱም እርሷን ተዋህደው ተነሥተው ተሸራሽረው ጸጥ ብለው ይቆማሉ ሕዝ.ምዕ ፴፯ ተመልከት እንዱ ከእንዱ በክብር ይበልጣል ያንዱ ከክብ ክብር ካንዱ ከክብ እንዲበልጥ ጻድቃንም በክብር ተበላለጠው ይነሣሉ ትንሣኤ ዘሊሚር የሚነሡ አሉ ትንሣኤ ዘለክብር የሚነሡ አሉ።

ስለሞቱ ሰዎች ተዝካር ማውጣት እንዲገባ ከዚህ ይናገራል ፀኤል (አስራኤል) ሰው የሞተባቸው እንደሆን ዕለቱን በቅናው በ፯ውም ቀን በ፲፪ ቀን በ፴ በ፹ በ፹ በመንፈቅ አስከ ዓመት እየሄዱ ሽቱ ያርከፈክፉ ነበር ሐዋርያት ለነፍስ መዓዛ ነፍስ ነው እንጂ መዓዛ ሥጋ ምን ይረባል ምን ይጠቅማል መሥዋዕት ሠዉላቸው ቁርባን አስቀርቡላቸው ዕጣን አሳጠኑላቸው ጻዊት አስደግሙላቸው ተዝካር አውጡላቸው ብለዋል ዕለት የወንድ ፫ት የሴት ፯ት የወንድ ፲፪ የሴት፴ የሴት፵ የወንድ፹የሴትመንፈት የወንድ ዓመት የሴት የነፍስስ ሌትና ወንድ የላትም ብሎ በፎት ቢታጉልበ ፯በ፯ ቢታጉል በ፲፪ በ፲፪ ቢታጉል በ፴ በ፴ ቢታጉል በ፵ በ፵ ቢታጉል በ ፹ በ፹ ቢታጉል በመንፈቅ በመንፈቅ ቢታጉል በዓመት ያድርጉላቸው ሲል ነዉ ዕለት አለ መጋቤ ዕለት ከክብ አለ ያን ላያውቅ ቢመጣ ዕዳ አትበልበት ሲሉ በፎት አለ ጌታ በፎቀን ተነሥቷልና የዚህ ምሳሌ ፯ት አለ የ፯ቱን ልውሳን ሥርዓት ላያውቅ ቢመጣ ዕዳ አትበልበት ሲሉ ፲፪አለ የ፲፪ን ሐዋርያት ያን ላያውቅ ቢመጣ ዕዳ አትበልበት ፴አለ መጋቤ አውራህ ከክብ አለ ይልቁንም አዳም ልጅነቱን አሰወስዶ ነበርና ዕዳ አትበልበት ሲሉ ፹ አለ ፀኤል (አስራኤል) ፹ቀን ሹቱ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ይቀቡ ነበርና መንፈቅ አለ ብርንናት በትሙት ፪ጊዜ ነው በዓመት አለ ፴ሲይ ዓውደ ዓመቱን የሚፈጽም በትሙት ፪ጊዜ ነውና ይህን ሳያውቅ ቢመጣ ፊኛ እትብልበት ሲሉ ነው፡ ፩እል (አስራኤል) ሰው የምትሻቸው እንደ ሀጎ አስካሎት ድረስ ከመታብር እየሄዱ ሽቱ ያደክርቡ ነበር ሐዋርያት ለነፍስ መዓዛ ነፍስ ነው እንጂ መዓዛ ሥጋ ምን ይፈባል ምን ይጠቅማል መሥዋዕት ሠውላችው ቁርባን አስቆርቡላችው ዕጣን አሳጥኑላችው ዳዊት አስደግሙላችው ብለዋል ሄሬም እኛ ፍትሐት የምናስፈታው ተዝካር የምናስወጣው የሐዋርያትን ቃል ይዘን ነው እንጂ ልብ ወለድ አይደለም ይህም እንዲገባ ቀሲፕንጠስ ሲናዶስ ፍትሐነገሥት አንቀጸ ሙታን መጫኔነት ነው ይህም ለሙታኑም ለሕያዋኑም ማለት ለአስቆራቢዎችም ክብር እንዳላቸው ጌታ ለቅዱስ ባርክ በራእይ ገልጾ አሳይቶታል ታላቅ ዙፍ በቅሉ ክንዱና ክንፉ ክአድማስ እስከ አድማስ ደርሶ ፍሬ አፍርቶ አዕዋፍ ሊመገቡት ክቢታቹ የመዓር የወተት ምንጭ ፈልቆላቸው ሕፃናት ሊጠቡት አይቷል ደንግጠ ተኛ ወዲያው ዛፉ ደርቆ አዕዋፍ ሲንጫጩ የማርና የወተቱ ምንጭ ደርቆ ሕፃናት ሲያለቅሱ ማየትህ ሙታን በሞቱበት ቀን ይመጣሉ መሥዋዕት የሠዉላቸው ቁርባን ያስቆረቡላቸው ዕጣን ያላጠኑላቸው ዳዊት ያስደግሙላቸው ተዝካር ያጠሙላቸው እንደሆነ ብድር መላሽ ይሰጣችሁ ክርስታችን ክገነት ከመንግሥተ ሰማያት ይከፈላችሁ ይተካላችሁ ብለው መርቀው ይሄዳሉ ፍትሐት ያላስፈቱላቸው ተዝካር ያላወጡላቸው እንደሆነ ግን ይህን ሁሉ ያላደረጉላቸው እንደሆነ ብድር መላሽ ይጎላችሁ ክርስታችን ክገነት ከመንግሥተ ሰማያት ይንቀላችሁ ብለው እረግመው ይሄዳሉ ስለዚህ ተዝካር አይጠቅምም ብለው የሚጠራጠሩ ሰዎች በጣም ይጉዳሉ ከዚህ በኋላ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ከሃሊነት ጌትነት ምሥጋና ገንዘቡ የሚሆን ጌታ በመጣ ጊዜ ለሁሉም እንደሥራው ክፉ ለሠራ ፍዳውን በጎ ለሠራ ዋጋውን ይክፍለዋል። ለዘለዓለም የማያልፍ ከሃሊነት ጌትነት መንግሥት የሚገባው ፈጣሪያችን ይክበር ይመስገን አሜን ::

ተፈጸመ በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም አመ ፲፱ ለወርኃ መስከረም በእለተ ረቡዕ በደብረ ሊባኖስ ርእሰ አድባራት አምደ ሃይማኖት አምላሊሃ ለኢየሩሳሌም አግዓዚት ዘተርጉመ ታኅሣ ወአባሲ መምህር ጥበቡ ንብረማርያም አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን።

ከዚህ ቀጥሎ ረድኡተ እግዚአብሔርን ጽግ በማድረግ የበስመ አብን ትርጉም እንጀምራለን ወጣኒውም ፈጻሚው እርሱ እግዚአብሔር ቅዱስ
ነውና ለመፈጸም ያብቃን
እንዲል የጀመረውን ሥራ እግዚአብሔር የሚፈጽምለት ሰው ንዑድ ክቡር ነው መፈጸም እንጂ መጀመር አያስደንቅምና የምንሠራውን ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ከፍጻሜ ያድርስልን አሜን።

ማለት ዓለም ሳይፈጠር ሥላሴ በፈቃነት በቦነት ሊሰለስቡበት፣ ሊቀደሱበት፣ ሊጠሩበት ዛራም በዚህ ዓለም ሲሰለስቡበት፣ ሲቀደሱበት፣ ሊጠሩበት የሚኖሩ ኋላም ማለት ከአሰተ ምዕአት በኋላ ሊሰለስቡበት፣ ሊቀደሱበት የሚኖሩ "ር" ስማቸው ነው ይህንስ በስመ አብ ማን ተናግሮታል ቢሉ ቅዱስ ጴጥሮስ በናህለ ኢዮጴ ሳለ ከሥዕሉ አርዕስት ሊመለከት አግኝቶ ተናግሮታል ምነው አሱማ ከተናገረው አይጽፈውም ነበር ቢሉ እርሱስ አይቶ ተናገረው እንጂ አልጻፈውም እንኪያ ማን ጸፈው ቢሉ ፫፻፲ሊቃውንት ጽፈውታል እነርሱስ ከምን አግኝተው ጽፈውታል ቢሉ መከስምያኖስ ሩፑትልጥያኖስ የሚባሉ ሁለት ዓላውያን ነገሥታት ተነስተው

ብለው አዋጅ ነገሩ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ ማለት ተተኮሱ መጻሕፍትም ተቃጠሉ ተቆነጻጸሉ ምዕመናንም የሚሞቱ ሞቱ የተሰደዱም ተሰደዱ ዘመኑም ፱ዘመን ይሆናል ከመከራው ጽናት የተነሳ ዘመነ ሰማዕታት ተብሏል ተባርዮን የማያስቀር ጌታ ራትዕ ንጉሥ መፍቀሬ ሃይማኖት ቁስጠንጢኖስን አነገሠ እነርሱም ቀርነ ሃይማኖት ጸንቶለታልና ብሉ አዋጁን በአዋጅ መልሶታል።

ከመሆኑ እርዮስ ወልድ ፍጡር በመሰኰቱ ብሉ ተነሥቷል ፫፻፲፰ ሲቃውንት በኒቅያ ተሰብስበው አርዮስን አውግዘው ለይተው ሃይማኖትን አጽንተው ሥርዓቱንም ሲሠሩበት ጊዜ ሕግ ሲያግጉ ሲደነግጉ መጻሕፍትን ሲሰበስቡ ፵ዘመን የሸነቡ ገናብ ብራናውን ሳያርሰው ቀለሙን ሳይደመስሰው አግኝተው ሥጻሕፍት ሁሉ አርዕስት ይሁን ሲሉ ብለው ተናግረውታል ጽፈውታል። ጌታም በማቴምስ ወንጌል መእዝዘታጠምቅምሙ በሉ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ትርጓሜውም በስመ አብ ማለት የአብ ያለህ ማለት ነው ወልድ ማለት የወልድ ያለህ ማለት ነው መንፈስ ቅዱስ ማለት የመንፈስ ቅዱስ ያለህ ማለት ነው ቦ በአብ ስም አምንን አዘን ወላዲ ብለን በወልድ ስም አምንን ወልድን ተውላዲ ብለን በመንፈስ ቅዱስ ስም አምንን መንፈስ ቅዱስን ሠራዒ ብለን በስም በግብር በአካል ይት ስላልን በባሕርይ በሕልውና በአገዛዝ በመናዘዝ በመስክት ይቱን ጸ አምላክ ብለን እናምናለን ፩ አምላክ ማለት ቅድመ ዓለም የነበረ በማዕከለ ዓለም ያለ ይህን ዓለም አሳልፎ የሚኖር ማለት ነው ምንም ለአዘጋይቱ አካላት ይት ብንል እግዚአብሔር ጽም ይት፡ም ነው ምንም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ቢል እግዚአብሔር የይቱ ስም ነው አንስ ሶበ አዜ አግዚአብሔር አብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አንጺል ሃይማኖተ አበው ስለዚህ የክርስቲያን ልጅ ሁሉ ተጉቶ አድሮ ከመኝታው ሲነሣ በስመ አብ መወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ብሎ ገጹን አማትበ መኑግት ይገባዋል ስንኒን መንፈላዊ ሥጋዊ ነገርም ቢሆን በስመ አብ ላይባል አይጀመርምና የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወገኖች ሁሉ ሴትም ወንድም ቢሆን በሺት ዓመት ይህም ባይሆን በ፲፪ ዓመት የነፍስ አባት "መምህረ ንስሐ" ይሠ ጸም መጽም ጸሎት መጸለይ ስግደት መስገድ ይገባል በክርስቲያን ሃይማኖት አምኖ ከተጠመቀ በኋላ የክርስቲያን ሥራ ካልሠሩ ክርስቲያን አይባልም ሃይማኖትም ጥምቀትም አንድ ነው ቦ ጉባኤ ቃለ እግዚአብሔር በተጀመረ ጊዜ አጋንንት እንቅልፍ እንቅልፍ ለማለት ላለማለማት ይመጣሉና ስሚውም አለሚውም በስመ አብ ብሎ መጀመር ይገባል በቅድስት ሥላሴ በሥላሴ ስም አምነን ጉባዔ በምናስተምርበት ጊዜ ምዕመናን ለመስማት ሲቀርቡ አጋንንት ለማሳት እንዳይኑርቡ በስመ አብ ብሎ መጀመር ይገባል ሥላሴንስ ስለምን ቅድስት አላቸው ቢሉ በሴት አንቀጽ መሰላቸው ሴቶች ወላድያነ ሕጻናት ናቸው ሥላሴም ፈጣሪያነ ዓለማት ናቸውና ቦ ሴቶች ከማኅፀናቸው ልጅ ፍሬ ያስገኛሉ ሥላሴም ከባህርያቸው ፍጥረትን ሁሉ ያስገኛሉና በ ሴቶች ፈጭተው ጋግረው ጠምቀው ሁሉን ይመግባሉ ሥላሴም በገነም አብቅለው በዐሐይ አብስለው በነፋስ ለይተው ፍጥረትን ሁሉ ይመግባሉና ቦ ሴቶች ርኅሩሃተ ልብ ናቸው ሥላሴም ርኅሩሃን ናቸውና ሥላሴ አድመ ምሕረት አሉት ስመዩ በስመ ብእሲት እንዲል እንዘአአምን ወአትመሐፀን እከህደከ ሰይጣን በትድመ ዛቲ አምየ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዚች ንዕድ ክብርት ልዕልት በምትሆን በእናቱ በቤተ ክርስቲያን ፊት ቆሜ ለይጣን ባላጋራየን አክደዋለሁ አሸሪዋለሁ ቦ ክጀህለሁ ሽሬህለሁ ማለት ነው ለይጣን ባላጋራን

ሊዘጹት እንዲት ነው ቢሉ ሥራውን "ንብራን" ትዮ ነው የሰይጣን ባላጋራ ሥራው "ንብሩ" ምንድነው ቢሉ ሐሚት ስሰት ትዕቢት ፍትረ ገፎይ ጸሊእ ቢጽ አምልኮ ባዕድ ነው ይህን ሥራውን ሳይተዉ እከህደከ ሰይጣን ቢሉ አይለትም አያርትም አሁን ሰው እንሩን በእግር ብረት እጁን በሰንሰለት አሰረው ሃያ ቢሉት ይሄዳልን ይህም እንደዚያው ነው ይህን ሥራውን "ንብሩ" ትዮ ግን ነከደከ ሰይጣን ቢሉት እንደጠለሰ ተኖ አንድተም በኖ ይጠፋል እንት ያሉት ሰምዕያ ማርያም ጽዮን ለዓለመ ዓለም ጸወንም" ይላል ይህች የዘለዓለም ምስክሯ የምትሆን ድንግል ማርያም የዘለዓለም መመክያዬ የምትሆን ድንግል ማርያም" ናዝሬት የዘለዓለም ምስክሯ በዙሪም ያስተረጉማል ይህን ማለት አምላ መጠቢያ ማለት ነው አምላ መጠቢያ ከሌት ቁር ከቀን ሐሩር ከቀን ወራሪ ከሌት ሰባሪ ያድናል እመቤታችንም ከሥጋዊ ጠላት ከአገር አጋንንት ከገዳነው አሳት ታድናለችና እምኀ መጠቢያ ይላታል የእመቤታችንንም ሰሚን ጠርቶ ስመ ትርጓሜዋን ላይናገሩ መሄድ እያገባምና ከዚህ ይናገራል "ሩታኤል" ማርያም ማለት ውሀበት ሀብተ እግዚአብሔር ማለት ነው ለእግዚአብሔር ስቡ ሆና ተሰጥታለችና ጸጋ ወሀብት ማለት ነው ለጊዜው ለእናት ለአባቷ ጸጋ ወሀብት ሆና ተሰጥታለች ፍጻሜው ግን ለሁላችን ናትና ዘ ንጽሕት ማለት ነው ለጊዜው ዘር ካሰቀ ደም ከደረቀ በኋላ ተመልሳ እናት አባቷን ደስ አሰኝታቸዋለች ፍጻሜው ግን ንጽሐ ሥጋ ከንጽሐ ነፍስ አስተባብራ ይዛ ተገኝታ የሥላሴ ማደሪያ ሆናለችና ቦ ኮሰአሊተ እግዚአብሔር መሰብአ ማለት ነው የሰውን ልመና ወደ እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ምሕረት ወደ ሰው እያመላለሰች ታማልዳለችና ለሰውስ ይሁን ለእግዚአብሔርን ያለው እንዴት ነው ቢሉ ንጽሕ ጠብቆ መኖር እግዚአብሔርን ማገልገል ነውና ቦ ቅድስት ክብርት ማለት ነው ከተለዩ የተለየች ከክብሩ የክብረች ማለት ነው ቦ እግዝእተ መላእክት መሰብእ ማለት ነው ለሰውም ለመላእክትም ታማልዳለችና ለሰውስ ይሁን ለመላእክት ማማለዷ እንደምን ነው ቢሉ ተውስቦ የሚባል መልአክ ድኖባታልና ቦ ፍሥሕት ማለት ነው ሰኑጥአን ሥርየት ለጻድቃን ዕሴት ታሰጣለችና ቦ ተፈ.ሥሐ ቤተ ጰሁዳ ሠጥኃሠጺ ቤተ ጸኤል (አስራኤል) ማለት ነው ፲፪ቱ ነገድ ሁሉ በአሷ አምነው ደስ ብሏቸዋልና ቦ መርህ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው ምዕመናንን ሁሉ እየመራች ገነት ታገባተዋለችና ሚርያም ብሂልመርህ ለመንግሥተ ሰማያት እንጂል ቦ ማኅበረ መጎይምናን መመጎይምናት ማለት ነው ሰዊሮስ ዘእስሙናይን ማኅበረ መጎይምናን መመጎይምናት ብሎ እንደተረጐማት ቦ ልዕልት ማለት ነው

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ርም አርያም ማለት ነው ለቡል ልዕልት ማለት እንደሆነ እመቤታችንም መትህተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ናትና ምስጋናዋም ከምስጋና ሁሉ በላይ ነውና ቦ እግረ ፀሐይ ሰረገላ ፀሐይ ማለት ነው አስቴር ማለት እግረ ፀሐይ፣ ሰረገላ ፀሐይ ማለት እንደሆነ ቦ እመ ውኁዳን ማለት ነው አብርሃም ማለት አበ ውኁዳን ማለት እንደሆነ ቦ እመ ብዙኃን ማለት ነው አብርሃም ማለት አበ ብዙኃን ማለት እንደሆነ ይህንማ እንጂ ዘበአብራይስጥ ማሪሃም አይለውም ብሉ ማርያም ቅሉ እግዝአ ብዙኃን ማለት ነው ይዙም ስሟ በተወለደች በስምንት ቀን በቤተ ግዝረት እናትና አባቷ ማርያም ብለው ያወጡላት ስም ነው ሲያወጡላትም ከምድር ማርን ከገነት ያምን አምጥተው ማርያም ብለው አውጥተውላታል በምድር ካሉ መባልዕት ማርን በጣዕም የሚተካከለው የለም በገነት ካሉ አእዋፍ ያምን በመዓዛ የሚተካከለው የለም እሷንም በምድር ከደቂቀ አዳም በሰማይ ከመላዕክት አንቺ ትበልጪአለሽ ሊሉ ከምድር ማርን ከገነት ያምን አምጥተው አውጥተውላታል ቦ በሀገረ ትርጓሜ ማ ብሂል ማኅደረ መለኮት ር ብሂል ርግብየ ይቤለ ያ ብሂል ያንተዓፁ ኅቤሂ ኩሉ ፍጥረት ያ ብሂል ምስአል ወምስጋድ ወምስተሥራየ ኩሉ ኃጢአት ማለት ነው የእመቤታችን ስሟ ማለት ስመ ትርጓሜዋ ሰማይ ምድር ብራና አዕባን መድምዕ ዕፀው አብራዕ አብሕርት ቀለማት መላእክት ደቂቀ አዳም ጸሐፍት ቢሆኑ ባላለቀም ነበር ከብዙ በጥቂቱ ከምሉዕ በከፊሉ አድርጐ ጽፎታል ተናግሮታል እንጂ ነእኩተከ እግዚእ ወንሴብሐከ ንባርከከ እግዚኦ ወንትአመነከ አቤቱ ፈጽመን እናመሰግንሃለን እናምንብሃለን ንገኒ ለኪ አ ዘለከ አቤቱ መገባት ለሚገባህ ለአንተ እንገባልሃለን ይሰግድ ኩሉ ብርክ የለው ሁሉ ብርክ ልቦና ለአንተ ይሰግዳል፡ ስግደት ሠሦስት ወገን ነው አድንኖ፣ አስተብርኮ ስግደት ነው አድንኖ ያንገት አስተብርኮ የጉልበት ስግደት የመሬት ነው አድንኖ የሚለው እንገትን ዘንበል አድርጉ መስገድ አስተብርኮ የሚለው "ጉልበትን" በጉልበት ተንበርክኮ መስገድ ነው ስግደት ሦዝገን መሬት አስነክቶ ከመሬት ተደፍቶ መስገድ ነው፡ ወለከ ይትቀነይ ኩሉ ልሳን የሸፈቱ ሥነ ፍጥረት አንደበት ከምስጋና ጋራ ለአንተ ይገባል አንተ ውእቱ አምላክ አማልክት ያማልክት ሁሉ ፈጣሪ አንተ ነህ አማልክት የተባሉ መላዕክት ናቸው ወእግዚአ አጋዕዝት ገዢ ነኝ የሚል ሁሉ ገዢ አንተ ነህ ወንጉሠ ነገሥት የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ አንተ ነህ ነገሥታቱን የምትሾም፣ የምትሽር አንተ ነህ አምላክ አንተ ለኩሉ ዘሥጋ ወለኩላ ዘነፍስ የሥጋዊ የደማዊ ፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ አንተ ነህ ወንጹውዓነ በከመ መሐረነ ቅዱስ ወልድከ ንጹሕ

ፅኑዕ ዝኩር ልዩ የሚሆን የባሕርይ ልጅነ እንዳለተማረን በጸሎት እንጠራሀለን ጸሎትም ማለት የተበደለ ሰው ከንጉሥ ዛዴ እንዲጮኽ ወደ እግዚአብሔር የሚጮሁት ጩኸት ነው ዳግመኛ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው የሚፀልይ ሰው ቦጥ ብሎ ቆሞ መሰመን ነው እንጂ በእግር ወዲያና ወዲህ ማለት በዓይን ወዲህና ወዲህ ማየት አይገባም እንዘ ይብል እንዲህ ብሎ አንትሙሰ ዕበ ትጸልዩ ከመገሠ በሉ እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ እንዲህ በሉ አቡነ ዘበሰማያት የሰማይ አባታችን እናመሰግንሀለን ያትሥዲስ ዕምነ

ስምህ ይክበር ይመስገን ትምጻ መንግሥትከ መንግሥቱ ሰማያት ትሰጠን ወይኩን ፈቃድከ ልናመሰግንህ ፈቃድህ ያለ'ን በነው በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለሰለትነ ነገን ዩም መሰንክት በሰማይ አመስግነውህ ያው ምግብ ሆኗቸው እንዲሁ እናም በዚህ ዓለም አንተን አመስግንንህ የዕለት ምግባችንን ስጠን ኅደ ሃ ሰንሰባነነ ወጌጋየነ ዘመንግነኒ ንጎድግ ለዘእበሰለነ ነበደለንን ይትር ንሂያ ኑል አንተም በደላችንን ይቅር በለን እታብለነ እግዚኦ ውስተ መገሰ አቤቱ ወደ መከራ ወደፈተና አታግባን አሳ አድግነነ ርዛ ይብነ አጋዥኮ እኮይ ከክፉ ነገር ሁሉ አድነን እንጂ አሰመ ዚአነ ይእቲ ኑግንሥ ኃይል ወስብሐት ለዓለም ዓለም። ለዘለዓለም ያማሃለክ ክብር ከሀሊነት ጌትነት መንግሥት ያንተ ንገዘብ ነውና በአሙነት አ ይኑ።

በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልእክቱ አ እግዚአብሔር ማርያም ሰላም ለኪ እመቤታችን መልእክቱ ቅዱስ ገብርኤል ሰላም ብሎ እትፍሥሕንነሽ እኛም እናመሰግንሻለን ድንግል በሕሊናኪ ወድንግል ከሥጋኪ ሰመ እግዚአብሔር ፀባዖት ሰላም ለኪ በድንጋሌ ሥጋ ወደምጋል ነፍስ የጸናሽ ያአሸናፊ የእግዚአብሔር እናቱ እመቤታችን ሰላምታ ይገባሻል አንስት መቤታችን አንቺ ከሌቶች ሁሉ ተለይተሽ ርተባረክሽ ነሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን አያግለድሽ የምታስጪነሽ ወቡሩክ ፍሬ ክርሥቲ የማኅፀንሽም ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ በረከተ ሥጋን በረከተ ነፍስን የሚያድል ነው ቅዱሳኒሁ ፍሥሕት አ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስኪ ምልዕት ክብር ሆይ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነስቶ ከአንቺ ጋራ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኗልና ደስ ይበልሽ ጸልዪ ወስአሊ ስለ ዎስፈረታ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመይሥረይ ለነ ኀጣውኢነ

Scanned by DocumentScanner | Lufick

ኃጢአታችን ያስተሠርይልን ዘንድ ባንቺ ተማፅነናልና ከልጅሽ ከወዳጅሽ ከፈጣሪያችን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታን ለምኝልን ቸር ነውና ይቅር ይበለን አሜን::

በአንድም ሳይሆን በነጠላው ተርጉሜዋለሁ በዚህ የምትጸልዩ ሁሉ እኔንም አትርሱኝ::

እነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል
እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው
ልዑል እግዚአብሔር እኛንም ሀገራችንንም ይባርክ
ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አሜን!

ኃጥእ ወአባሲ መምህር ጥበቡ ገብረማርያም የወንጌል ምርኮኛ

አሳታሚ:- መጋቤ ሃይማኖት ቀሲስ መንግሥቱ ጥላሁን

Scanned by DocumentScanner | Lufick